ሁለተኛው ጦርነት የለጨቦ ጦርነት ሲባል የሊብዶን ወገን የመራው የጦር መሪ ለጨቦ አጃቾ[23] ተብሎ ይጠራል። በለጨቦ አንጃንቾ የሚመረው የሊብዶ ጦር እጅግ ጠንካራ ስለነበረ የአካባቢው የአፌ-ታሪክ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙ ንጉሥ ምኒልክ እራሳቸው የሸዋን ጦር ይዘው በ1882 ዓ.ም. ወደ ሊብዶ ዘምተዋል። ይህ ጦርነት በሊብዶ ደበና በሚባል ቦታ የተደረገ ጦርነት ሲሆን በጦርነቱም የሊብዶ ጦር መሪ የነበሩት ለጨቦ አንጃንቾ ሊገዳሉ ችለዋል። በለጨቦ አንጃንቾ ሞት የሊብዶ ህዝብ ከተሸነፉ በኋላ በህዝቡ በጣም ከፍተኛ የሆነ የግፍ አገዳደል፣ ዘረፋ እና የቤት ቃጠሎ ወንጀሎች ተፈጽመዋል። በዚህ ጦርነት ወቅት በርካታ የሊብዶ ሀዲያዎች ወደ ቆሼ አካባቢ ሊሰደዱ ችለዋል። ከዚያም የሊብዶ ህዝብ ማሴቦ ቡርካሞ /Maasseebo Burkammo/ የተባለ ሽማግሌን መሪው አድርጎ በመምረጥ የሊብዶን ህዝብ ወክሎ ከምኒልክ ጋር እርቅ እንዲፈጸም አድርጓል።

የቀቤና እና የሊብዶ ሀዲያ በምኒልክ ወራሪ ሠራዊት ቁጥጥር ስር መውደቅ የተቀረውን የሀዲያ ህዝብ በቀላሉ ለማስገበር የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለታል። ሆኖም ግን ዋናውን የሀዲያ አካባቢ (ደቡብ ሀዲያ) ለመቆጣጠር የሸዋ ወራሪ ሀይል እንቅስቃሴ የጀመረው ከ1886 ጀምሮ ነበረ። በመሀሉ ግን የሀሰን ኤንጃሞ ሃይማኖታዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ /ጂሃድ/ በተቀረው ሀዲያ ላይ የተጀመረውን ዘመቻ እንዲቋረጥ አስገድዷል።

ለምሳሌ፣ ክበሞ (2007፡61) እንደገለፀው፣ በ1886 ዓ.ም. ራስ ጐበና ቀድመው ከተያዙት የሶዶ ጉራጌ አካባቢዎች

[23] ለጨቦ አጃቾ እና ለጨቦ አንጃንቾ የሚለዉ አንድ ግለሰብን እንደሆነ ይገመታል (ኤደሞ 1999) ፡፡





የተዉጣጣውን ሀይል ከራሳቸው ሠራዊት ጋር አንድ ላይ በማድረግ ወደ ሻሾጐ /Shaashoogo/ ሀዲያ ዘመቻ አድርገዋል። ከዚህ የሸዋ ወራሪ ሀይል ዘመቻ ጥቂት ቀደም ብሎ ሻሾጐ /Shaashoogo/ ከከምባታ ጋር ከፍተኛ ጦርነት በማድረግ በቡችሞ /Buchchamo/ ጦር ግንባር አሸናፊ ሆኖ ነበረ። በዚህም ምክንያት የራስ ጐበና ሀይሎች ወደ ሻሾጐ በሚደርስበት ወቅት የሻሾጐ የጦር መሪዎችና ትልልቅ ሽማግሌዎች ከከምባታ ጋር የተፈጠረውን አለመግባባት በእርቅ ለመፍታት ለመቻ /La'mmachcha/ በሚባል ቦታ ላይ የእርቅ ጉባኤ እያካሄዱ ነበረ። በመሆኑም የሻሾጐ አባገዳና ሌሎችም የጦር መሪዎች አለመኖር የአካባቢውን ተራ ህዝብ በቀላሉ እንዲሸነፍና እንዲበዘበዝ ዕድል ፈጥሯዋል።

በዚህ ሁኔታ የሻሾጐ አካባቢ በቀላሉ በጐበና ቁጥጥር ሥር ሲወድቅ አባገዳ ጌዶ በሽሮን /Abaagada Geedo Bashiiro/ በመምረጥ ለምኒልክ መንግሥት ሊገብር እንደተስማማ ገልፀዋል። አባገዳ ጌዶ በሽሮንም የሸሾጐ ባለበት በማድረግ ራስ ጐበና ሾመዋቸዋል። ይህ ሁኔታ ግን ሀሰን ኤንጃሞ በቀለቀለው የቀቤና ሀዲያዎች ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ምክንያት በመቀየር ቀቤና ተመላሶ በምኒልክ ሃይሎች ቁጥጥር ሥር እስከሚወድቅበት እስከ 1889 ዓ.ም. ድረስ ሻሾጐ ነፃ አካባቢ ሆኖ ቆይቷል። ከዚያም በ1892 ዓ.ም. በደጃዝማች ወልደ አሻግሬና በደጃዝማች ወዳጆ የተመራ የሸዋ ሀይል የሻሾጐን አካባቢ መልሶ ሊቆጣጠረው ችሏል። ከዚያም አባገዳ ሆስሶ /Abagada Hosiso/ የሻሾጐ ባለባት ተደርገው ተሹመዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ደጃዝማች ወልዴ አሻግሬ በ1886 ዓ.ም. የሌሞን ሀዲያ ለመቆጣጠር ዘመቻ ከፍቷል። ለዚህም ዘመቻ

ከሶዶ ጉራጌ አካባቢ የተዉጣጣ በርካታ ሰራዊት አሰልፏል፡፡ ነገር ግን በመሀሉ በሀሰን ኤንጃሞ የተቀሰቀሰው የቀቤና አመጽ የወልዴ አሻግሬን ትኩረትና ጥረት ወደ ቀቤና እንዲያቀና አስገድዶታል፡፡ ለቀቤና መሸነፍ በኋላ የደጃዝማች ወልዴ አሻግሬ ትኩረት እንደገና ወደ ተቀረው የሀዲያ አካባቢ ሲሆን የመጀመሪያ ተጠቂ የነበረውም የሌሞ ሀዲያ ህዝብ ነበር፡፡

በ1891 ዓ.ም. የሀዲያ ሽማግሌዎች እንደሚያስታውሱት የሌሞና የባዶጐ ሀዲያዎች የደጃዝማች ወልዴ አሻግሬን ዳግም ዘመቻ ለመቋቋም በህብረት ተሰልፈው ነበረ፡፡ ነገር ግን ይህ የተቃውሞ ህብረት ወራሪውን ሀይል ለረጅም ጊዜ ተቋቁሞ ሊያቆየው አልቻለም፡፡ ፊት ለፊት በሚደረገው ጦርነት ላይ ወራሪው ሀይል ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀ ስለነበረ የበላይነቱን ሲወስድ የሌሞና የሻሾጐ ሀዲያዎች የደፈጣ ውጊያን እንደ መጨረሻ የመከላከል አማረጭ ተጠቅመው እንደነበረ የአካባቢው ሽማግሌዎች ያስታውሳሉ፡፡ በመጨረሻም የሌሞ ገራድ የነበሩት ኦርሴ ቢብሶ /Orse Biib-biso/ ለደጃዝማች ወልዴ አሻግሬ በሰላም እጅ በመስጠትና በአጸፋውም የሌሞ ባለባት በመሆን ጦርነት እንዲያበቃ በማድረግ የገባርነት ዘመን እንዲጀመር ሆኗል፡፡

የሌሞና የባዶጐ ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላ ተስፋዬ (1993፡158) እንደገለፀው የአካባቢው ገዥ የሆነው ደጃዝማች ወዳጆ ጉበና የራስ ጉበና ዳጬ ልጅ የመጀመሪያውን ከተማ በሊሙ ውስጥ መጀመሪያ ባልቡላ /Baalbula/ ወይም ደማላ /Damaala/ ከዚያ ቀጥሎ አና /Aanna/ በተባለ የሌሞ ተራራ ላይ ሊመሠርት ችሏል፡፡ እነዚህ የአስተዳደርና የሠራዊት መቀመጫ የሆኑት ከተሞች በሀዲያና በከምባታ አካባቢ





የመጀመሪያዎቹ ከተሞች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ክበሞ (2007፡64) እንደጻፈው የመጀመሪያውን የአስተዳደር ከተማ በባልቡላ (Balbula) ወይም ደማላ (Damaalla) ከዚያም በአና /Aanna/ ላይ የመሰረቱት ደጃዝማች በሻህ አቦዬ ናቸው[24]፡፡

የሌሞ /Leemo/ ሀዲያዎች በኦርሴ ቢብሶ /Orse Biibbiso/ መሪነት ዘመን ወደ ገባርነት መቀየራቸው ቢነገርም ከወራሪው የሸዋ ሠራዊት ጋር ከፍተኛ ጦርነት ከገጠሙት የሌሞ መሪዎች ውስጥ አድል አዳና /Adil Ada/ እና አድል ፍርጦም /Adil Firxo/ ይጠቀሳሉ፡፡

ይህ በሌሞና በባዶጐ የተፈጠረው ሁኔታ በሌሎች የሰሜንና የምስራቅ ሀዲያ አካባቢዎች ከተከሰተው ገባርነትና የሸዋ የበላይነት ጋር ተዳምሮ የሶሮ /Sooro/ ሀዲያዎች ያለአንዳች ረዳትና አማራጭ ተስፋ በሚያስቆርጥ ከበባ ውስጥ እንዲወድቁ አስገድዷቸዋል፡፡ የሸዋ ሀይሎች በሶሮ ሀዲያ ላይ የነበራቸውን ከበባ ጠንካራ ያደረገው ሌላው ክስተት የከምባታ ህዝብ ከሸዋ ገዥ መደብ ጋር ከረጅም ዘመን ጀምሮ የነበራቸው ወዳጅነት ነው፡፡ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ቢሆንም የሶሮ ህዝብ በአጋጐና /Agaago/ በደዳች ያርሼ /Daddaachch Yaarshee/ መሪነት ከፍተኛ የመከላከል ጦርነቶችን አካሄዷል፡፡

[24] ላጵሶ (1982፡ 95) እንደገለፀዉ ከምኒልክ የወረራ ጦርነት በኋላ የዛሬዉ የሀዲያና የከምባታ ሕዝብ የሚኖርበት አካባቢ ከምባታ፤ ሌሞና ሻሾጎ ተብለዉ የሁለት ልዩ ደጃዝማች አገር ተደረገ፡፡ በደቡብ ...ከምባታ... የደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ ግዛት ተደረገ፡፡ ደጃዝማቹም አንገጫን የግዛቱ ከተማ አድርጎ ቆረቆረ፡፡ በሰሜንና በምዕራብ ሌሞ፤ ኮንተብ እና /ሶሮ/ ወረዳዎች በአንድነት ሌሞና ሻሾጎ ተብለዉ የደጃዝማች ባሻህ አቦዬ ግዛት ተደረገ፡፡ ደጃዝማች ባሻህ ከዛሬዉ የንግስት እሌኒ ሆስፒታል በስተምስራቅ በምገኘዉ አምባ ላይ ኣናን የግዛቱ ከተማ አድርጎ ቆረቆረ፡፡

የሶሮ ሀዲያዎች ካደረጎቸዉ ከባድ የመከላከል ጦርነቶች መካከል በሶሮና በጠንባሮ መካከል በሚገኛው የጐጐ ተራራ ላይ የሶሮ ሀዲያዎች በደጃዝማች ወልዴ አሻግሬ ከሚመራውና ከአጠቃላይ በወቅቱ ገባር ከተደረጉት አካባቢዎች ከተዉጣጣውና ከሸዋ ሰራዊት ጋር ያደረጉት ጦርነት ይጠቀሳል፡፡ በዚህም ጦርነት የሶሮ /Sooro/ ሀዲያዎች በሸዋ ሀይሎች ሊሸነፉ ችለዋል፡፡

በመሆኑም 1893 ዓ.ም. ከባደዋቾ /Baadawwaachcho/ ውጪ ያለው አጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ በሸዋ ወራሪ ሀይል ቁጥጥር ስር በመውደቅ ገባር እንዲሆን ተገዷል፡፡ የባደዋቾ /Baadawwaachcho/ ሀዲያዎች የምኒልክን ወራሪ የመቋቋም ትግል እስከ 1894 ዓ.ም. ድረስ ሊዘልቅ የቻለና እጅግ ከባድ ተብለው ከሚጠቀሱት የምኒልክ የወራሪ ሙከራዎች ውስጥ ሊጠቃለል የሚችል ነው፡፡ የምኒልክ የጦር አበጋዞች የነበሩት በዘመኑ በሀዲያና በከምባታ አካባቢ ይንቀሳቀሱ የነበሩት ደጃዝማቾችና ራሶች፤ ለምሳሌ፣ ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ፣ ደጃዝማች ወዳጆ ጐበና፣ ራስ መንገሻ አትከም በጋራም ሆነ በግል የባደዋቾን /Baadawwaachcho/ ሀዲያ ከወላይታ ህዝብ ጋር አንድ ላይ ለማስገበርና የጭቆና ቀንበር ለመጫን ያደረጉት ትግል በቀላሉ ሊሳካ አልቻለም፡፡

በመሆኑም በመጨረሻ ላይ በባደዋቾ ሀዲያና በወላይታ ላይ ንጉሥ ምኒልክ ራሳቸው መዝመታቸው ይታወሳል፡፡ ሁኔታውን ተስፋዬ (1993፡164) አለቃ ገብረስላሴን በመጥቀስ እንዳስቀመጠው:-





> *የአፄ ምኒልክ /ዳግማዊ/ የታሪክ ፀሐፊ አለቃ ገብረ ሥላሴ እንደዘገቡትም አፄው ከሸዋ ህዳር 16 ቀን 1894 ዓ.ም. ተነስተው በጌኛ /ሶዶ/፣ በማረቆ፣ በስልጤ፣ በሁልባረግ፣ በሀዲያ፣ በከንባታ አድርገው ወደ ባደዋቾ ሀዲያ ሕዝብ ክልል ሾኔና ቆርጋ ሲደርሱ ጦረኛውና ጀግናው የባደዋቾ ህዝብ በጨበጣ ውጊያ ጭምር ከፍተኛ ጦርነት እንደገጠማቸው ያወሳሉ፡፡*

በመሆኑም የምኒልክን የወላይታ ዘመቻ ውጤታማ ለማድረግ ከወላይታው በንጉሥ ጦና ከተመረው ከፍተኛ የተጋድሎ ጦርነት ቀድሞ የገጠማቸው የባደዋቾ /Baadawwaachcho/ ሀዲያዎች ከላይ በተገለፀው ሁኔታ በጀግንነት ያደረጉት ውጊያ ነበረ፡፡

በአጭሩ በባደዋቾ ከሀዲያዎች ጋር የተደረገው ጦርነት ውጤቱ ለወላይታ ዘመቻ መንገድ ከፋች ነበረ፡፡ በባደዋቾ ሀዲያ ላይ የተደረገውን ጦርነት የመሩት ንጉሥ ሚኒልክ መጀመሪያ የሰፈሩት በባደዋቾ ቀጣ /qaxxa/ በሚባል ቦታ እንደነበረ የአካባቢው ሽማግሌዎች ያወሳሉ፡፡ ቀጣ ከዛሬ የሾኔ ከተማ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ጉብታ ነው፡፡

የባደዋቾ ሀዲያዎች የንጉስ ምኒልክ ሰራዊት በጨበጣ ውጊያ ጭምር በተዋጉባቸው ጦርነቶችና ከዚያም በኋላ በወላይታ ከንጉስ ጦና ጐን በመሰለፍ ከፍተኛ ትግል ካደረጉት የባደዋቾ የጦር መሪዎች መካከል ጋጥአን /gaaxxanni/ ገትሶ ባለንጐ /Gatiso Baallango/፣ ጋጥአን ሰንዳቦ ብጃሞ /Gaaxxanni Sandaabo Bijaamo/ እና ጋጥአን ፈጂሶ ጎዴ /Gaaxxanni Faajjisso Godde/ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ጋጥአና (Gaaxxanni) በሀዲያ የጦር አበጋዝ የሚለውን ማዕረግ ይወክላል፡፡ የባደዋቾ ሀዲያዎች በንጉሥ ምኒልክ

በሚመራውና ዘመናዊ መሳሪያ ከታጠቀዉ እጅግ ከፍተኛ ጦር ከተሸነፉ በኋላ ወደ ወላይታ በማፈግፈግ ከወለይታ ህዝብ ጋር ከንዳቸውን በማስተባበር የወላይታው ጆግና ንጉሥ ጦና እስከተያዙበትና የወላይታ ዘመቻ እስካበቃበት ጊዜ ድረስ ተዋግተዋል።

በመሆኑም የባደዋቾ ሀዲያዎች የመጨረሻው ሽንፈትና ወደ ገባርነት መግባት የሚጀምረው ከወላይታ ሽንፈት ጋር ተያይዞ ይሆናል። ከ1894 በኋላ የባዳዋቾ ሀዲያዎች በሶስት ባላባቶች ተከፋፍለው እንዲገብሩ ተደርገዋል። እነዚህም ባላባቶች ቀኛዝማች ወራቆ /woraaqo/፣ ቀኛዝማች ጢቀሞና /xiiqqamo/ እና ቀኛዝማች ሀርቦሮ /Hirbòoro/ ናቸው።

በአጠቃላይ ከ1886-1894 ዓ.ም. ባለው ጊዜ አጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ በንጉስ ምኒልክ ወራሪ ሀይል ቁጥጥር ስር ሊወድቅ ችሏል[25]።

የሀዲያ ህዝብ በዘመናት ማንነቱን አስጠብቆ ለማቆየት ያደረገውን ጠንካራ ትግልና በርካታ ጦርነቶችን በመመልከት ከንጉስ ምኒልክ ወራሪ ሀይልም ጋር ያደረገውና ረጅም ጊዜ የፈጀው ጦርነት የዚሁ የዘመናት ታሪኩ አካል አድርጐ ለመመልከት ያስገድዳል። የትኛውም የሀዲያ ጊቾ /Giichcho/ የሚችለውን ያክል ትግል በማድረግ ስለተሸነፈ ብቻ የንጉስ ምኒልክን ወራሪ ሃይሎች የበላይነት እንደተቀበሉ መረዳት ይቻላል። ሆኖም ግን ንጉስ ምኒልክ በሀዲያ ላይ

[25] ላጵሶ ( 1982፣ 96) ሰንጠረዥ 19 ላይ ወደ ሀዲያ ከዘመቱት የምኒልክ የዘመን የጦር አበጋዞች መካከል ንጉስ ምኒልክን ራሳቸዉን፣ ራስ ወልዴ፣ ራስ ጎበና፣ ደጃች ገርማሜ፣ራስ መኮንን፣ ቀኛዝማች ዉቤ፣ ፊታዉራሪ ሀብተጊዮርጊስ፣እና ደጃች ወዳጆ ተጠቅሰዋል።





የተጠቀሙት አዲስ የጦርነት ስልት ንጉሱ ከነበራቸው የመሳሪያ የበላይነትና የተሻለ የጦርነት ልምድ እንዲሁም በዘመኑ ተከስቶ ከነበረው የከብት በሽታና የፈንጣጣ ወረርሽኝ ጋር ተዳምሮ የሸዋ ሀይሎች ለረጅም ጊዜ የቆየ ገባርነትን በሀዲያ ህዝብ ላይ እንዲጭኑ ዕድል ፈጥሯል።

በጦር መሣሪያ የነበራቸው የበላይነት፣ በተለይም ለዘመኑ ዘመናዊ የነበሩትን መሣሪያዎች መጠቀም መቻላቸው ካለብዙ ጉዳትና የሠራዊት እልቅት በአጭር ጊዜ ድል እንዲቀዳጁ አስችሏቸዋል። በጣም የቆየ የጦርነት ልምድ ያላቸው የወራሪው ሃይል መሪዎችም ተራ ስህተቶችን በማስወገድ ተገቢውን የጦርነት ስልት በመከተል ለተገኘው ድል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በዘመኑ ተከስቶ የነበረው በሽታ የሀዲያን ህዝብ ዋነኛ የሀብቱ መገለጫና የኑሮው መሠረት የሆነውን ከብቱን በማውደም ደሃ ከማድረጉና ከማሽማቀቁም በላይ በወሳኝ ጦርነቶች የሚጠቀሙት የጋማ ከብቶችን እንዲያጣ አድርጓል። በተለይም በዘመኑ የተከሰተው የፈንጣጣ በሽታ የሰው ሀይል ሀብቱን ወይንም ዋነኛ ሰራዊቱ እንዲመናመን አድርጓል።

እላይ ከተጠቀሱት ሁሉ ግን የምኒልክ ሰራዊት በሀዲያ ህዝብ ላይ የተከተለው የጦርነት ስልት/tactic/ ለድሉ ከፍተኛውን ሚና እንደተጫወተ የሀዲያ ሽማግሌዎች ይገልፃሉ። ይህ የወረራ ጦርነት የሀዲያን ህዝብ እንደ አንድ ህዝብ በመውሰድ በአጠቃላይ ህዝቡ ላይ በአንድነት የታወጀ ጦርነት ሳይሆን እያንዳንዱ የሀዲያ ጊቾን /Giichcho/ በተናጠል ተራ በተራ በማስገበር፣ የሀዲያን ህዝብ የአንድነት ጥንካሬን በማመንመን የተካሄደ ነበር።

በዚህም መሰረት ዘመቻዎች ሲደረጉ በቀቤና፣ በማረቆ፣በሌሞ፣ በሻሾጎ፣ በሶሮ፣ በባደዋቾ በተሰይ በእያንዳንዳቸው ታውጆ ሲሆን እስትራቴጂውም በጂኦግራፊ አቀማመጥ አቅጣጫ ከሰሜን እያደገ እንዲሄድ ተደርጎ የተሸነፈውና የገበረው የሀዲያ ጊቾ /Giichcho/ ቀጣይ ጦርነት ወደታወጀበትና ወንድሙ ወደሆነው ሌላው ጊቾ በባለባቶች መሪነት ህዝቡን ይዞ እንዲዘምትና እንዲወጋ ይደረጋል። ይህንንም በማድረግ በቀድሞ የአንድነት ስሜት ፈንታ የጠላትነትና የልዩነት ስሜት በተግባር ስር እንዲሰድ ተደርጓል። የዚህ ተመሳሳይ እስትራቴጂ አካል የነበረውና ሌላው ዘዴ በሀዲያ ዙሪያ ያሉትን ጎረቤት ማህበረሰቦች ሀዲያን ለማስገበር በሚደረገው ጦርነት ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ተገደዋል። ከዚህ የተነሳ በሀዲያና በአንዳንድ የጎረቤት ማህበረሰቦች መካከል የጠላትነት ስሜት እንዲፈጠር ከፍተኛ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል።

የሀዲያ ህዝብ እጅግ ጠንካራና አሸናፊ የነበረው በረጅም ታሪኩ እንደ አንድ ህዝብ ባደረጋቸው ተገድሎዎች ነበረ። በንጉስ ምኒልክ ዘመን በተደረገው የወረራና የማስገበር ጦርነት ግን ሀዲያ ያሉትን ያከል ጊቾዎች /Giichchuwwa/ እራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ጦርነቶች ተደርገዋል። ይህ ሁኔታ፣ ጊቾዎች የየራሳቸው የሆነ የግል ታሪክና ልምድ እንዲኖራቸው በማድረጉ የነበራቸውን የአንድነትና የወንድማማችነት ስሜት አቀዛቅዟል። ይህ ወራሪው ሀይል የተከተለው እስትራቴጂ ቀጥሎ ባዋቀረውም የጭቆና አስተዳደራዊ ሥርዓት ተጠናክሮ በመቀጠሉ ሥርዓቱን በጋራ በመቋቋም ፈንታ እርስ በርሳቸው በጥርጣሬ እንዲተያዩ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል።





የንጉስ ምኒልክ ወራሪ ሀይል ከላይ የተጠቀሰውን ወሳኝ የጦርነት ስልት /ታክቲክ/ በመከተል በሀዲያ ህዝብ ላይ ከባድ የጭቆና ቀንበር በዘመኑ እንዲጭን ምቹ ሁኔታን የፈጠረው ውስጣዊ ሁኔታ እንደነበረ ይገለፃል። ምቹ ሁኔታ ነበረ ተብሎ በህዝቡ የሚገለፀው ከ17ኛው ክፍለ ዘመን የሁለተኛው አጋማሽ ጀምሮ በዛሬው የሀዲያ ህዝብ መኖሪያ አካባቢ የተከማቸው ጠንካራው የሀዲያ ሀይል ለረጅም ዘመናት ያለጠንካራ የውጭ ችግርና ጦርነት የተረጋጋ ኑሮ በመሠረተበት ዘመናት በውስጥ በጊቾዎች /Giichchuwwa/ መካከል ቀስ በቀስ እያደገ የመጣው የፉክክር ስሜት ነዉ። ይህን በሀዲያ ጊቾዎች መካከል በሰላማዊ ወቅት የተፈጠረውን ነባራዊ ምቹ ሁኔታ የምኒልክ ወራሪ ሀይሎች በተገቢው መንገድ ለአላማቸው ዘላቂ ስኬት ወደሚያገለግል አሰመግባባትና የእርስ በርስ ጦርነት ሊቀይሩት ችለዋል።

### 2.6.1. *ሀዲያ* ከ1894-1935 ዓ.ም.

የሀዲያ ህዝብ በአጼ ምኒልክ ዳግማዊ ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ አካባቢውን የሚያስተዳድሩ የተለያዩ ሰዎች ከሸዋ ሲመደቡለት ቆይቷል። ከአድዋ ጦርነት በፊት በነበሩት ጥቂት ኣመታት ማለትም 1893 - 1896 ዓ.ም. ውስጥ ደጃዝማች ወዳጆ ጉበና፣ ደጃዝማች በሻህ አቦዬ /የአጼ ሚኒልክ የአክስት ልጅ/ ፣ እና ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ /የንጉሥ ሳህለሥላሴ የልጅ ልጅ የራስ ዳርጌ ልጅ/ አካባቢውን አስተዳድረዋል። ይህ ከላይ የተጠቀሱት የአጼ ሚኒልክ ደጃዝማች ተሿሚዎች ያስተዳድሩ የነበሩት የአስተዳደር አካባቢ በጥቅሉ ከምባታ፣ ሌሞና ሻሾጉ ተብሎ ይጠራ እንደነበረ ክበሞ (2007፡74) ገልጿል።

ከምባታ በሚባለው በዚህ የአስተዳደር ክፍል ውስጥ ከሀዲያ ዋና ጌቾዎች ውስጥ የባደዋቾ ጌቾ /Güchcho/ በአጠቃላይ ሲቂ በሚባል ተገቢ ባልሆነ ስም እንዲወከል ተደርጓል። የተቀረው የዛሬዉ የሀዲያ ህዝብ (ሶሮ፣ ሌሞ፣ ባዶጐ፣ ሻሸጐ) በአንድ ላይ ሌሞ በሚሰው ክፍል እንዲወከሉ በማድረግ ቀድሞ ያልነበረ አጠቃላይ ማንነትን ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል። ሌሞ የሚለው መጠሪያ ከላይ ለተጠቀሱት የሀዲያ ጌቾዎች የተሰጠበት ምክንያት የአስተዳደሩ ከተማ በሚገኝበት ጌቾ /Güchcho/ ስም ነው ተብሎ ቢወስድ እንኳ'ን ህዝበ ተገቢ እና ሁሉን የሚያቅፍ የጥንት የማንነቱ መገለጫ የሆነውን ስሙን እንዳይጠቀም እንደተደረገ መመልከት ይቻላል። እንዲያውም ጨቋኙ ፊውዳላዊ አስተዳደር በሂዳት ሀዲያነትን ሊያመለክት የሚችል ስም በምንም መልኩ ጐልቶ እንዳይወጣ እንዳደረገ መረዳት ይቻላል።

በአድዋ ጦርነት ወቅት ባሻህ አቦዬ የሌሞ ገዥ የነበሩ ሲሆን የአካባቢውን ህዝብ ለ1896 ዓ.ም. የአድዋ ጦርነት መርተው ወደ ሰሜን ዘምተዋል። ይህ የአካባቢው ገዥ የነበሩት ግሰሰብ በጦርነቱ ህይወታቸውን በማጣታቸው ከአድዋ መልስ ለአካባቢው አዲስ አስተዳዳሪ ተመድቧል። በመሆኑም ከአድዋ ጦርነት በኋላ በ1897 ዓ.ም. ራስ አባተ ቧያለው የከንባታ እና ሌሞ አውራጃ ገዥ ተደርጐ በመሾም በ1900 ዓ.ም. የአውራጃውን ዋና ከተማ የዛሬው የሀዲያ ዞን ዋና ከተማ በሆነችው ሆሳዕና መሥርቷል።

ይህ ዛሬ ሆሳዕና የተባለው ከተማ የተቆረቆረበት ቦታ በአዲስ ስም ከመሰየሙ በፊት የአካባቢው ህዝብ ሴች ዱና /sechch duuna/ ብሎ ይጠራ እንደነበረ ይነገራል። የራስ አባተ ቧያለው አስተዳደር በሸዋ መንግሥት ውስጥ በተፈጠረው





ውስጣዊ ችግር (ባህሩ 1991፣ 120-121) ራስ አባተ እስከታሰረበት እስከ 1909 ዓ.ም. ለ12 ዓመታት አካባቢ ቀጥሏል። ከዚያ በኋላ ራስ አጥናፍ ሰገድ ልዑል ሰገድ፣ ደጃዝማች ወልደገብርኤል በሻህ፣ ራስ አባተ ጌታቸው እና ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ እና ሌሎችም የአስተዳደር አካባቢውን ገዝተዋል።

ከራስ አባተ ቧያለው እስር በኋላ በሸዋ መንግሥት ውስጥ የተፈጠረውን የስልጣን ሽኩቻና ትግል እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የሀዲያ ህዝብ በገዥው የንጉስ ምኒልክ መንግስት ላይ የአመጽ እንቅስቃሴ ጀምሮ ነበር። ይህ የሀዲያ ህዝብ የአመጽ እንቅስቀሴ በአካባቢው ወዳሉት ሌሎች ማህበረሰቦችም በተለይም ጉራጌ፣ አሩሲ ኦሮሞ እና ወላይታ ሊዛመት መቻሉ'ን የአካባቢው ሽማግሌዎች ይናገራሉ። ከዚህም የተነሳ ራስ አባተ ቧያለው ከስልጣኑ ተነስቶ መቅደላ ላይ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1919 ዓ.ም. ድረስ የሸዋ አስተዳደር በሀዲያ ህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞ እና ትግል እየገጠመው ቀጥሏል (ብሬውካምፑር 1980፡436)። በወቅቱ ታዋቂ ከነበሩት ግጭቶች መካከል በሀላባና በሻሸጐ ሀዲያ፣ በወላይታና በባደዋቾ ሀዲያ፣ በጉራጌና በባዶጐ ሀዲያ ፣ እንዲሁም በከምባታና በሶሮ ሀዲያ መካከል የነበሩት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

በ1919 ዓ.ም. የአካባቢው አስተዳዳሪ ሆኖ ተመድቦ በመሥራት ላይ የነበረው ራስ ጌታቸው አባተ የሀዲያን ህዝብ አመጽና ተቃውሞ በመቆጣጠር በአካባቢው የሸዋን ስርአት ዳግም እንዲጠናከር አድርጓል። የተቃውሞ አመጽ ለማቆም በተደረገው ጭካኔ በተሞላበት እርምጃ የአመጽ መሪ የነበሩ ግለሰቦች ንብረታቸው ተዘርፏል፤ አንዳንዶቹ በገበያ ቦታዎች በስቅለት እንዲቀጡ ተደርገዋል።

በአጠቃላይ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ በንጉሥ ምኒልክ ወደ ሀዲያ የገባው ጨቋኝ ስርአት በአስተዳደራዊ መዋቅሩ ሀዲያ የሚለውን የሀዝቡን አጠቃላይ መጠሪያ በማንኛውም አጋጣሚ ለመጠቀም ፈቃደኛ ሳይሆን ቀጥሏል፡፡

በምኒልክ ወረራ ምክንያት ወደ ደቡብ በአጠቃላይና ወደ ሀዲያም አዲስ ከመጡት ክስተቶች የሚጠቀሰው የነፍጠኛ የባለባትና የገባር ስርአት ነው፡፡ ባለባት ከወረራ በኋላ የተወሰነውን የሀዲያ ሀዝብ ክፍል በመምራት ወይም በመወከል አዲስ ከመጣው ኃይል ጋር አብረው ለመሥራት የተስማሙ የቀድሞ ገራዶች ወይም ዳናዎች /Daannuwwa/ ሲሆኑ የአሸናፊው የሸዋ መንግሥት ተባባሪ ሆነው የቀጠሉ የሀዲያ ሹመኞችን ይመለከታል፡፡

በዚህ አዲስ በመጣው ሥርዓት የሀዲያ አጠቃላይ መሬት የመንግስትና የባለባት መሬት በመባል ለሁለት በዋናነት ተከፍሏል፡፡ ምንም እንኳን መሬቱ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ለሁለት ይከፈል እንጂ በአጠቃላይ መሬት ላይ የበላይ ባለስልጣን ከሸዋ የተመደበው የአካባቢው ገዥ ነበረ፡፡ የመንግስት መሬት በጦርነት ወቅትና ከዚያም በኋላ ወደ አካባቢው በመጡ ነፍጠኞችና በመልከኞች እጅ የተያዘ ነበረ፡፡ ከእነዚህ የተረፈው መሬት ለየጉሳው ባላባቶች የተከፋፈለ ነበረ፡፡ በዚህ መሰረት አጠቃላይ የዛሬው የሀዲያ ዞን በዚያን ዘመን በብዙ የባለባት አካባቢዎች የተከፋፈለ ነበረ፡፡ በሀዲያ ውስጥ ታዋቂ ከነበሩት ባለባቶች መካከልም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከታች የተመለከተው የባላባቶች ዝርዝር በአጠቃላይ የባላባታዊ ሥርዓት ዘመን ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ በሥርዓቱ የባላባትነት ማዕረግ ያገኙትንና መረጃው የተገኘላቸውን ሰዎች ብቻ ያጠቃልላል፡፡





1. ቀኛዝማች ስዩም አኖሬ
2. ቀኛዝማች ኑራሞ
3. ግራዝማች ሱጵሶ
4. ግራዝማች ሀይሌ
5. ቀኛዝማች ወራቆ
6. ቀኛዝማች ጢቃሞ ዱጉኖ
7. ቀኛዝማች ሀርበሬ አማዶ
8. ቀኛዝማች ቂንጣሞ ሶበቆ
9. ቀኛዝማች ተፈሶ ብልጢቦ
10. ግራዝማች ቀጸኖ
11. አድል[26] አኖሬ አደዬ
12. ቀኛዝማች ሀንቆሬ
13. ግራዝማች ገደቦ
14. ግራዝማች ዳድቼ ሱዱቦ
15. ዳኛ ኤርሞሎ ሀንድሶ
16. አድል ማሞ አኖሬ
17. ፊታውራሪ ጋረዶ ሆገሶ
18. የተከበሩ ፀደቀ ጋረዶ
19. የተከበሩ ጌታቸው ሀይሌ
20. ቀኛዝማች ሱምበሶ ሀንቆሬ
21. ፊታውራሪ ዱታሞ
22. ፊታውራሪ ሀንድሶ
23. ፊታውራሪ ጌጃ ገሪቦ
24. ደዳች መልስቦ

[26] በዚህ ዝርዝር ከተጠቀሱት የመእረግ ስሞች መካከል አንዳንዶቹ ለምሳሌ አድል፣ ደዳች የሀዲያን ባህላዊ መእረግ ሳይተዉ ባለባት የሆኑትን ግለሰቦች ያመለክታል፡፡

ከሁሉም የነፍጠኛው ስርአት ውጤቶች የከፋው አዲስ የመጣ የሸዋ ጨቋኝ ስርአት የሀዲያን ባህላዊ ሴራንና የአሰራር ስርዓቱን በእጅጉ እንዲዳከም አድርጐ ማለፉ ነው። ይህ የዘመኑ ስርዓት በሀዲያ ሴራ ላይ ያሳድር የነበረውን ጫና በመቋቋም የሀዲያን ሴራ መሠረታዊ መርሆዎች ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ የሀዲያ ባላባቶች የራሳቸውን ባህላዊ ዳኛ በመምረጥ በመካከላቸው ይፈጠር የነበረውን ችግር ይፈቱ ነበረ። ለምሳሌ፣ ቀኛዝማች ቂንጣሞ /በንጉሥ ሃይለ ሥላሴ የዋገበታ ባላባትነት የተሰጣቸውና በሀብታቸው ብዛት የከንባታን አውራጃ በመወከል ከንጉሱ እጅ ማዕረግ፣ ኒሸንና ካባ የተሸለሙት/ የሶሮ ባላባቶች ባህላዊ ዳኛ ሆነው ያገለግሉ እንደነበረ በዘመኑ የነበሩ ሽማግሌዎች ያስታውሳሉ።

## 2.6.2 የሀዲያ ህዝብ በጣሊያን ወረራ ዘመን

የጣሊያን ፋሽስት መንግስት በአድዋ ጦርነት ወቅት በኢትዮጵያውያን ጀግኖች እጅ የደረሰበትን አሳፋሪ ሽንፈት ለመበቀልና በሌሎችም በርካታ ምክንያቶች[27] በ1935/36 በኢትዮጵያ ላይ እጅግ የተጠናከረና ከባድ ወረራ ፈጽሟል። ለዚህ የ1935/36 የጣልያንና የኢትዮጵያ ጦርነት በግንባር ቀደምትነት ከዘመቱት ኢትዮጵያውያን ሃይሎች የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝብ በአከባቢው ባለባቶችና በሸዋን መንግሥትን ተሿሚ አስተዳዳሪዎች በመመራት ያደረጉት ተጋድሎ ይጠቀሳል።

የሀዲያና የከምባታ ህዝብ ለዚሁ ጦርነት በደጃዝማች መሸሻ ወልዴ (የደጃዝማች ወልደ አሻግሬ ልጅ) መሪነት ወደ ሰሜኑ

[27] የሞሶሎኒ የአዉሮፓ ፖሊሲ በተለይም አዉስትሪያ ላይ ያነሳዉ የዘረኝነት ጥያቄ በሂትለር ዉድቅ መደረግ ኢትዮጵያን ለመዉረር እንድወስን እንዳደረገዉ ባሁሩ (2005: 153) ገልጿል።





የጦር ግንባር ተንቀሳቅሷል። ከሀዲያና ከከምባታ የተነሳው ሠራዊት መጀመሪያ አዲስ አበባ ላይ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢና በዛሬው ጌጃ ሠፈር ተብሎ በሚጠረው አካባቢ ሰፍሯል። ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ ጌጃ ሠፈር ተብሎ የሚጠራው አካባቢ በጦርነቱ ወቅት የሀዲያን ክፍለ ጦር የመሩት ፊታውራሪ ጌጃ ገሪቦ /Geejja Garibo/ ከነሠራዊታቸው እንዲሰፍሩ የተመሩበት አካባቢ ነበረ። ከዚያም የሀዲያና የከምባታ ሰራዊት ወደ ሰሜን የጦር ግንባር በመንቀሳቀስ በተንቤን ግንባር በመሰለፍ የመጀመሪያው የጣሊያን የተጠናከረ ሀይል ሰለባና የግፍ አገዳደል ገፈት ቀማሽ ሊሆኑ ችለዋል።

በወቅቱ የጦርነቱን ሁኔታ በበቂ ማስረጃ የሚያስረዱ የሀዲያ ሽማግሌዎች ደጋግመው እንደሚገልጹት የሀዲያና የከምባታ ሠራዊት ከሁሉም የተንቤን ግንባር ተዋጊ ሀይሎች ፊት ለፊት ተሠልፈው ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው ነው። በጦርነቱ ወቅት የሻለቃና የሻምበል አዛዥ በመሆን ወደ ተንቤን ከዘመቱት ጀግና የሀዲያ ልጆች መካከል የሚከተሉትን ለምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

ፊታውራሪ ጋረዶ ጃባሞ
ቀኛዝማች ቀጸና ምሻሞ
ቀኛዝማች ሕርቦሮ
ቀኛዝማች ጢቀሞ ዱጉኖ
ቀኛዝማች ሀንድሶ
ፊታውራሪ ጌጃ ገሪቦ
እማም ኤርሞሎ
አድል ማሞ አኖሬ
ዳኛ ላምቤቦ ወራቆ

በተንቤን ጦር ግንባር በተደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ የሀዲያንና የከምባታን ሠራዊት መርተው የዘመቱት ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ በጠላት ጥይት ተመተው ሲወድቁ ለቀጣዮቹ ውጊያዎች የቀድሞ የከንባታና ሌሞ ገዥ የነበሩትና በጦርነቱ ወቅት የከፋ ጠቅላይ ግዛትን ሠራዊት ይመሩ የነበሩት ራስ ጌታቸው አባተ መሪ ተደርገው ተሹመዋል፡፡ በተንቤን ጦር ግንባር ሽንፈት የገጠመው የኢትዮጵያ ሠራዊት የመጨረሻ ውጊያ ለማድረግ ማይጨው ላይ ቢሰበሰብም በጦርነቱ ድል ሳይቀናው ተመልሷል፡፡

የሸዋው ነፍጠኛ መንግሥት አስተዳዳሪዎች ወደ ሰሜኑ ጦርነት ሠራዊታቸውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ የሀዲያና የከምባታ ህዝብ በወቅቱ በነበረው ጨቋኝ አስተዳደር ላይ ነበራቸውን አሉታዊ አመለካከት በአንክሮ ስለሚገነዘቡ በሆሳዕና ከተማ ላይ ወደ 500 የሚጠጋ ተጠባባቂ ጦር አስቀምጠው ነበረ የዘመቱት፡፡ በማይጨው ግንባር የኢትዮጵያ ሠራዊት መሸነፍንና ንጉስ ሃይለ ስላሴም ወደ ውጪ አገር መሰደዳቸውን የሀዲያ ገበሬዎች በሰሙበት ወቅት የሸዋ ነፍጠኛ አስተዳደርን ለመበቀልና ዳግም ወደ አካባቢው እንዳይመለስ ለማድረግ እጅግ የተጠናከረ የተቃውሞ ትግል ውስጥ ገቡ፡፡

ምንም እንኳን አካባቢውን ቂም ከቋጠሩት የሀዲያና የከምባታ ገበሬዎች እንዲጠብቁ የተመደቡት የነፈጠኛ ጥብቅ ጦር የተሻለ መሳሪያና የጦርነት ልምድ የነበራቸው ቢሆንም፣ የሀዲያ ገበሬዎች ግን በእጃቸው ያለውን ማንኛውንም ባህላዊ መሳሪያ በመጠቀምና በብዙ ቁጥር በማመጽ የሸዋን ነፍጠኞች ቤተሰቦች፣ ንብረታቸውንና ጥብቁን ጦር ከፍተኛ ጉዳት አድርሰውበታል፡፡





የማይጨውን ሽንፈትና የንጉሱን ወደ አውሮፓ የመሰደድ ወሬ ለሀዲያ ገበሬዎች በማያወላውል ማስረጃ ያደረሰውና ግጭቱ በይፋ እንዲጀመር መንገድ የከፈተው በጦርነቱ ተሳትፎ ሽንፈቱንም ተመልክቶ የተመለሰው አበጋዝ ጋድቾ ሄመቾ /Abagaaz Gaadichcho Heemachcho/ የተባለ ሀዲያ ነበረ፡፡ አበጋዝ ጋድቾ ሄመቾ በሶሮ የኦሞሾራ /Omoshora/ ቀበሌ ነዋሪ የነበረ ግለሰብ ነበረ፡፡ አበጋዝ ጋድቾ ወደ ሀዲያ ከደረሰ በኋላ ድሮውንም አመች ጊዜ ጠብቆ ለነበረው የሀዲያና የከምባታ ገባሮች የነፍጠኞችን መሰረት ከአካባቢው ለመናድ ወሳኝ ጊዜ መድረሱን በማስረዳት የአመጽ እንቅስቃሴን መምራት ጀምሯል፡፡

የአመጽ እንቅስቃሴው በግልጽ የተጀመረውና በሆሳዕና ከተማ ውስጥ ባሉት የነፍጠኛ ቤተሰቦች፣ንብረትና ጥብቅ ጦር ላይ በአበጋዝ ጋጅቾ ሄመቾ ጦርነት የተከፈተው በግንቦት 1936 ዓ.ም. ነበር፡፡ የሀዲያና የከምባታ ገባሮች ለረጅም አመታት በገዥዎች በደረሰባቸው ጭቆናና የበቀል ስሜት ብቻ በመነዳት የነፍጠኞችን ልጆችና ሚስቶች ገደሉ፡፡ ወንድ የሆነውን በመሰለብም ገዳይነታቸውን ለማስመስከሪያነት ተጠቀሙ፡፡ ይህ አሰቃቂና ጭካኔ የተሞላበት ግድያ፣ የቤት መቃጠልና ንብረት ማውደም ተግባር ማንም በበቂ ሁኔታ ሳይቆጣጠረዉ[28] ማይጨው የተሸነፈው የሀዲያና የከምባታ ሠራዊት ወደ አካባቢው እስከሚደርስ ድረስ ቀጥሏል፡፡

[28] በወቅቱ ከነፍጠኛዉ ስርኣት ተጠቃሚ የነበሩት አንዳንድ የሀዲያ ሽማግሌዎችና ተዋቂ ግለሰቦች በሀዲያ ዉስጥ ለነበሩት የነፍጠኞች ቤተሰብ ከለላ በመስጠት የሀዲያ ገባሮች ቁጣ እስከሚበርድ ደብቀዉ አቆይተዋቸዋል፡፡

ንጉሰ ነገስት አጼ ሀይለ ስላሴ ጣሊያኖች ድል ማድረጋቸውን በማረጋገጥ ወደ አውሮፓ ሲሰደዱ የሀዲያና የከምባታን ጦር ከደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ሞት በኋላ ሲመራ የነበረው ራስ ጌታቸው አባተም ከንጉሡ ጋር አብሮ ተሰደደ፡፡ በመሆኑም በጦርነቱ ወቅት ከመደምሰስ የተረፈው ጥቂት የሀዲያና የከምባታ ጦር በመልስ ጉዞ ወቅት የተመራው በእነ ፊታውራሪ ታምራት ወልደሰማያት አዝማችነት ነበረ፡፡ በመልስ ጉዞ ወቅት የሀዲያና የከምባታ ጦር በደጃዝማች ወልደማርያም ከሚመራው የጋሞ ጐፋ ጦር፣ በደጃዝማች መኮንን ወሰኑ ከሚመራው የወላይታ ጦርና ከሌሎችም የአካባቢው ተመላሽ ጦር ጋር በህብረት ነበር የተንቀሳቀሰው፡፡

የመልስ ጉዞ ያደርግ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት በተለያዩ ምክንያቶች በየመንገዱ በየአካባቢው ህዝቦች ከፍተኛ የሆነ የደፈጣ ውጊያ፣ ዝርፍያና፣ ሰለባ ይገጥመው እንደነበረ ሽማግሌዎች ያወሳሉ፡፡ በሀዲያ ውስጥ ከተፈጠሩት ተመሳሳይ አጋጣሚዎች የሚጠቀሰው የሊብዶ /Libido/ ወይም የማረቆ ሀዲያዎች በደጃዝማች ወልደ ፃድቅ ይመራ ከነበረው የአርሲ ተመላሽ ጦር ጋር የፈጠሩት ግጭት ነው፡፡ በዚህ ግጭት (ኤደሞ፣1999) ከ2000 የሚበልጥ የአርሲ ነፍጠኛ ሠራዊት ከነአዝማቹ በሊብዶ ሀዲያዎች እንደተደመሰሰ ይገልፃል፡፡

እንግዲህ ከላይ የተገለጹት በየአካባቢው ለምሳሌ በራያ፣ በወሎ፣ በሰሜን ሸዋ ከጦርነቱ መልስ የተከሰቱትን አደጋዎች አልፈው ወደ ሀዲያ የደረሱት የነፍጠኛው ሀይሎች በሀዲያ አካባቢ የጠበቃቸው እጅግ የተጠናከረ የአመፅ እንቅስቃሴ ነበረ፡፡ እነ ፊታውራሪ ታምራት ወልደ ሰማያትም ወደ አካባቢው ከደረሱ በኋላ የሁኔታውን አስከፊነት በመገንዘብና





አመጹ በእነርሱ ሀይል ብቻ ሊቆም የማይችል መሆኑን በመረዳት የሀዲያን ህዝብ አመፅ ለመቋቋም የሚያስችል ድጋፍ በሀዲያ አካባቢ ያሉትን ህዝቦችን የሚገዙ የሸዋ አስተዳዳሪዎች የሚገዙትን ህዝብ በመያዝ እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ በዚህ መሰረት የወላይታ፣ የስልጤና የሁልበረግ ባለባቶችና የጦር መሪዎች እንዲሁም ከማይጨው ሽንፈት በኋላ ከሀዲያና ከምባታ ጦር በህብረት በእነ ደጃዝማች ወልደማሪያምና ደጃዝማች መኮንን ወሰኑ ይመራ የነበረው ጦር የሀዲያን ህዝብ አመጽ ለመደምሰስ በህብረት ተሰልፈዋል፡፡

የሀዲያ ህዝብ በነፍጠኛው ሥርዓት ላይ የቀሰቀሰውን አመጽ ለመደምሰስ የወላይታ ህዝብ በፊተውራሪ ጭንቃቶ በካሎና በፊታውራሪ ዘሜና በመመራት የነፍጠኛውን ስርአት በመደገፍ በሀዲያ ህዝብ ላይ ዘምቷል፡፡ የስልጤንና የሁልባረግን ህዝብ በማምረት በሀዲያ ጭቁን ህዝብ ላይ ነፍጠኛን በማገዝ የዘመቱት ጎልቤ ዱቢሶና ኢማም ሱጋቶ ነበሩ፡፡

የሀዲያን ህዝብ የአመጽ እንቅስቃሴ በተለያዩ አካባቢዎች ከአበጋዝ ጋድቾ ጋር በመሆን ከመሩት መካከል ጋጠን / Gaaxxann/ አልከሞ ምሴ፣ ጋጠን /Gaaxxan/ ምርከና እጃጆና ጋጠን /Gaaxxann/ ባርጎጆ ሀዳቼ ይጠቀሳሉ፡፡

በመጨረሻም ከላይ የተጠቀሰው የተባበረው ሀይልና የሀዲያ አማጽያን በሆሳዕና አጠገብ ባቴና /Baateena/ ወንዝ ላይ በተደረገው ጦርነት የሀዲያን ገባሮች ድል በማድረጉ አበጋዝ ጋዲቾ ወደ አሞሸራ ሲያፈገፍግ የሆሳዕናን ከተማ ነፍጠኞች

መልሰው በመቆጣጠር የቀረውን ቤተሰቦቻቸውንና ንብረታቸውን ከሞትና ከውድመት ሊታደጉ በቅተዋል። አበጋዝ ጋዲቾ ከኦሞሾራ የነፍጠኞች ጥቃት ለማምለጥ ወደ ግቤ በረሃ በመሸሽ እስከ 1937 ዓ.ም. ድረስ እዚያው ተደብቆ ቆይቷል።

የሆሳዕና ከተማ በነፍጠኞች እጅ ዳግም መውደቅን ተከትሎ በሀዲያ ላይ ይህ ነው የማይባል የቅጣት እርምጃ ተወስዷል። በጣም ብዙ ሀዲያ በነፍጠኞች የተገደሉ ሲሆን የበርካቶች ቤታቸው ተቀጥሏል፣ ንብረታቸውም ተዘርፏል። የሸዋ ነፍጠኞች በሀዲያ ህዝብ ላይ የበላይነትን ለመመለስ እንዲችሉ ከፍተኛውን እገዛ ያደረገው የአካባቢውን ብሄሮች የራሳቸው ደጋፊዎች በማድረግ ከሀዲያ ብሔር ጋር እንዲዋጉ ማድረግ መቻላቸው ነው። ከማይጨው ሽንፈት በኋላ የሀዲያ ጭቁን ህዝብ ያደረገው ትግልና የመጨረሻ ዕድሉን ብረውካምፔሪና ጥላሁን (1999፡ 23) እንደሚከተሰዉ ገልጸዋል።

> *ጣሊያኖች የረጅም ጊዜ /የአድዋ/ አፍረት ቅማቸውን ለመበቀል በ1935 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ በከፋቱት ጦርነት እውን ማድረግ እንደጀመሩ የሸዋ ንጉሳዊ ስርአት በሀዲያ ላይ የነበረው አገዛዝ ችግር ላይ መውደቅ ጀምሯል። በአገሪቱ የነበሩት የአማራ ሰፈሪ ሠራዊት ከየአካባቢው ወደ ሰሜኑና ወደ ምስራቁ ጦር ግንባሮች ተንቀሳቅሰው ከወራሪው የፋሽስት ጦር ጋር እንድዋጉ ተደርጓል። የየአካባቢው ባለባቶችና ገባሮች የተለያዩ አገልግሎችን በጦር ግንባሩ ለመስጠት ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ወደተጠቀሱት የጦር ግንባሮች ተንቀሳቅሰዋል። በ1936 ዓ.ም. የጸደይ ወራት የኢትዮጵያ ጦር በሁሉቱም የጦር ግንባሮች መሸነፍ የመጀመሩ ወሬ ወደ ሀዲያና ወደ ሌሎችም የደቡብ አካባቢዎች ሲደርስ የሀዲያ ህዝብ የነፍጠኞችን ቤተሰብና ጥቅም*





> *ለማስከበር ወደ ጦር ግንባር ሳይዘምቱ እዚያው ሲጠብቁ በነበሩት የነፍጠኛ ጥብቅ ሀይል ማመጽ ጀምሯል። ምንም እንኳን ጠመንጃ የታጠቁ ቢሆኑም የሀዲያ ህዝብ የቁጥር የበላይነትን በመጠቀም ባሉት የአካባቢው መሳሪያዎች በነፍጠኛ ቤተሰብና ንብረት ላይ ባደረሰው ጥቃት አካባቢውን ሲገዙ የነበሩትን ብዙ ሰዎችን ጨምሮ ብዙ ሴቶቻቸውና ልጆቻቸው በአመጺው የሀዲያ ገባሮች እጅ ተገደሉ። በአጠቃላይ ግን የንጉሱ ሀይሎች በሀዲያ ህዝብ ላይ የአካባቢ ብሄሮችን በተለይም ወላይታና ስልጤን በማነሳሳት ጭምር በዳረጉት ጦርነት የቀድሞ የበላይነታቸውን ሊመልሱት ችለዋል።*

በ1937 ዓ.ም. የጣሊያን ወራሪ ሀይል የሀዲያን አካባቢ ከተቆጣጠረ በኋላ በተመሳሳይ ዓመት መጋቢት ወር ላይ የሆሳዕና ከተማ የጣሊያን የአካባቢው አስተዳደር መቀመጫ ተደረገ። ከዚያም የአካባቢው የጣሊያን ኮሚሺነር /ምስሴ/ የሀዲያ አካባቢ አማጽያንና ሽፍቶች እጃቸውን በሰላማዊ መንገድ በመስጠት ሰላማዊ ኑሮ መጀመር እንደሚችሉ ጥሪ አቀረበ። ይህንን ጥሪ በመቀበልና ከነፍጠኞች ጋር ያደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ በጣሊያን አስተዳደር እንደውለታ ይቆጠራል ብሎ በማሰብ አበጋዝ ጋድቾ ሄመቾም ለጣሊያን አስተዳደር እጁን ሰጠ። በተቃራኒዉ የጋድቾን ታማኝነት ከቀድሞ የአመጽ ታሪኩ ጋር በማነጻጸር የተጠራጠረው የጣሊያን የአካባቢው አስተዳደር አበጋዝ ጋድቾ ሄመቾን ከወንድሙ ከግራዝማች መርሻ ጋር በሆሳዕና ከተማ በሴች ዱና ጉብታ ላይ ተረሽነው እንዲገደሉ አድርጓል።

በጦርነቶቹ መጨረሻ ላይ ከሀዲያ እና ከከምባታ የተወጣጡና በእነ ቀኛዝማች ጨፋሞ አምበሌ የሚመራው የአስታራቂ ሽማግሌዎች ቡድን የነፍጠኛ ተወካዮችንና በጦርነቱ ወቅትም

ወቅትም ወሳኝ ሚና የተጫወቱትን እነ ፊታውራሪ ታምራት ወልደ ለማያትንና ደጃዝማች መኮንን ወሰኑን በማነጋገርና ህዝቡን አዲስ የተፈጠረውን ሁኔታ በማሳመን በዳረጉት ጥረት በአካባቢው አንፃራዊ ሰላም እንዲፈጠር አድርገዋል።

## 2.6.3. በጣሊያን አስተዳደር ዘመን በሀዲያ የተከሰቱ ጊዜያዊና ዘላቂ ለዉጦች

ጣሊያን ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠረ በመሰረተው የአስተዳደር መዋቅር ከጣሊያን በፊት ከምባታና ሌሞ ይባል የነበረው አካባቢ፣ 1936 - 1938 ዓ.ም. ድረስ ሌሞ፣ ሻሾጐና ከምባታ የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል። ነገር ግን በ1937 ዓ.ም. ግንቦት ወር የጣሊያን ሠራዊት ወደ ሆሳዕና ሲደርስ፣ አብዛኞቹ የሀዲያ ባላባቶች ለአዲሶቹ ገዥዎች አጠራጣሪዎች በነበሩት ሁኔታ የከምባታ አጠቃላይ ብቸኛ ባላበት የነበሩት ፊታውራሪ በርገኖ ሞልሶ /woma/ ለጣሊያኖች በሰላም ስላገቡላቸውና ያለፈው ታሪካቸውም ለገዥ መደብ ምቹ ሆኖ ያለፈ በመሆኑ፣ በአካባቢው የጣሊያኖች ወኪል ለመሆን ችለዋል።

አብዛኞቹ የሀዲያ ሽማግሌዎች እንደሚገልጹት ወማ /woma/ በርገኖ ሞሊሶ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ምንም እንኳን ከምባታ ውስጥ በርካታ ታዋቂ የጐሳ መሪዎች በየአካባቢው ቢኖሩም ሌሎች ባላባት መሆን የሚገባቸውን ማዕረጉን እንዳያገኙ በማድረግ ብቸኛ የከምባታ ባላባት ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ ከ1939 ጀምሮ እስከ 1974 ዓ.ም. የዘለቀውን ከምባታ አውራጃ የሚል መጠሪያ በሀዲያ ህዝብ ላይ ጭምር እንዲጫን ትልቁን አስተዋጽኦ አድርገዋል። አካባቢው ከምባታ አውራጃ ወደሚለውና ከ1939-1974 ዓ.ም. ወደ ዘለቀው አስተዳደራዊ መጠሪያ እንዴት እንደተቀየረ ከበሞ (2007፡107) እንደሚከተለው አብራርቷል።





*... የዛሬው የሀዲያና የከምባታ አካባቢ መቼና ለምን ከምባታ አውራጃ ተብሎ መጠራት እንደጀመረ የሚያስረዱ ተገቢ የጽሁፍ ማስረጃዎች የሉንም። በአዲሱ የአስተዳደር መዋቅር አደረጃጀት ከምባታ አውራጃ የሚለው መጠሪያ ከምባታንና ሀዲያን ሁለቱን የሚወክል ሆኗል። ሆኖም ግን የአካባቢው ቃላዊ ማስረጃዎች ያለ ልዩነት እንደሚያስረዱት ይህ አዲሱ መጠሪያ እውን ሊሆን የቻለው የከምባታ ንጉሳዊ ቤተሰብ ለሸዋ ገዥ መደብ ባለው ታማኝነትና የቅርብ ትስስር ምክንያት ነው። በመጀመሪያው የንጉስ ምኒልክ ሁለተኛው ወረራ ወቅት የሀዲያ ህዝብ በባህላዊ መሪዎቻቸው ወይም ገራዶቻቸው መሪነት የንጉሡን የወረራ ጦርነት በመቃውም አስከፊ ጦርነቶችን ሲያደርጉ የከምባታ ንጉሳዊ ቤተሰብ በወማ /woma/ ወይም ንጉሥ ድልበቶ ደጉዮ መሪነት ህዝባቸውን ይዘው በሰላም ገብረዋል። የሀዲያ ህዝብ በንጉሥ ምኒልክ ወራሪ ሃይል ተሸንፎ ወደ ገባርነት ከተለወጠ በኋላ እንኳን የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም በነፍጠኞች ላይ በተደጋጋሚ ሲያምጽ ተመሳሳይ ሁኔታ በከምባታ ህዝብና መሪዎች ዘንድ አልታየም። ከዚህ በተጨማሪ ጣሊያን ወደ አካባቢው ሲደርስ የከምባታ ባለባት የነበሩት ፊታውራሪ በርገኖ ሞሊሶ ለጣሊያን በሰላማዊ መንገድ እጃቸውን ሰጥተው ገብተዋል። በዚህ ሁኔታ ፊታውራሪ በርገኖ ከአካባቢው የጣሊያን አስተዳዳሪዎች ጋርም ጥብቅ የሆነ ወዳጅነት ሊመሰርቱ ችለዋል። ይህንን አጋጣሚ በአግባቡ በመጠቀም የአካባቢውን የቀድሞ መጠሪያ በማስለወጥ ከምባታ አውራጃ እንዲባል አድርገዋል።*

ይህንኑ ተመሳሳይ ጉዳይ፣ ወይም የአካባቢው አስተዳደራዊ የመጠሪያ ስም በጣሊያን ወረራ ወቅት ወደ ከምባታ አውራጃነት መቀየሩንና ሂደቱን ተስፋዬ (1993፡ 231) እንደሚከተለው አስቀምጧል።

> *ኢትዮጵያ በ1936 ዓ.ም. በፋሽስት ኢጣሊያ ተወራ በተያዘችበትና በቅኝ ተገዥነት ቀንበር ሥር በወደቀችበት በአምስቱ አመታት ከ1936 – 1941 ዓ.ም. የከምባታ አስተዳደር ክልል ከ1936-1938 ዓ.ም. ድረስ ሌሞ፣ ሻሾጐና ከምባታ ተብሎ እንዲጠራ ተወስኖ እንደነበረ ሲታወቅ ከ1939-1941 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በግዛቱ ክልል የነበሩት ባላባቶች ሁሉ በከምባታው ባለበት ... የበላይነት ሥር እንዲተዳደሩ የፋሽስት መንግሥት ምስለኔ በመወሰኑ በርገኖ ሞሊሶ የነበራቸውን ሥልጣን በመጠቀም የግዛቱን መጠሪያ ወደ ጥንታዊው መጠሪያ እንዳስለወጡና ክልሉም ከምባታ ተብሎ እንዲጠራ እንዳስደረጉ የአካባቢው አዛውንት ያወሳሉ፡፡*

ከላይ ከተመስከተው የተስፋዬ (1993) ጽሁፍ መረዳት የሚቻለው የአካባቢው መጠሪያ በጣሊያን ወቅት እንኳን ሁለት ጊዜ መቀየሩን ብቻ ሳይሆን፣ የከምባታ ባለባት የነበሩ ፊታውራሪ በርገኖ ሞሊሶ የነበራቸውን ቅርበትና ታማኝነት እንደመልካም አጋጣሚ መጠቀማቸውን ነው፡፡ በመሆኑም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሀዲያ የሚለውን የህዝቡንና የአካባቢውን ትክክለኛ መጠሪያ የሸዋ ገዥ መደብ ፈጽሞ ለማጥፋት የሀዲያን ህዝብ በአጠቃላይ በተወሰነ ወቅት ሌሞ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌሞና ሻሸጐ አንዳንዶቹን በተለይ የባደዋቾን ሀዲያዎች ሲቄ፣ በማለት ዳር ዳር ሲል የነበረውን ዕቅዱን የጣሊያንን ፋሽስት ሃይል የበላይነት አጋጣሚ በመጠቀም ወደ ከምባታ አውራጃነት ሊያስቀይሩ ችለዋል፡፡

ምንም እንኳን የግዛቱ ጥንታዊ መጠሪያ ከምባታ ብቻ የሚል እንደነበረ የሚያስረዳ ተገቢ የሆነ ማስረጃ ማቅረብ ባይቻልም፣ የሀዲያ ህዝብ በአካባቢው ከጥንት ጀምሮ በሀያልነት (ብረውካምፔርና ጥላሁን 1999፡20 እና ብረውካምፔር 1980፡ 433) ይኖር እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ





የአካባቢውን መጠሪያ የከምባታ አውራጃ ወደሚለው ጥንታዊ መጠሪያ ፊታውራሪ በርገኖ እንዳስለወጡ እንዳወሱ ከላይ በተገለጸው ጸሀፊ የተጠቀሱት የሀዲያ ባላባት ቀኛዝማች ስዩም አኖሬ በተቃራኒው የአካባቢ መጠሪያ የከምባታ አውራጃ መባሉ ተገቢም ትክክልም አለመሆኑን በማመን ስህተቱን ለማስተካከል ሲታገሉ የኖሩ መሆናቸውን በርካታ የጽሁፍና የሰው ማስረጃዎች በማያወላውል ሁኔታ ያረጋግጣሉ፡፡

የጉዳዩን ትክክለኛ ገጽታ በተሳታፊነት ጭምር ከሚያስታውሱትና በአሁኑ ሰዓት በአዛውንት ዕድሜ ከሚገኙት የሀዲያ ሽማግሌዎች አንዱ የሆኑት ገራድ ወልደጊዮርጊስ ቂንጣሞ እንደሚያስረዱት ከላይ የተጠቀሱት ቀኛዝማች ስዩም አኖሬ ከሌሎችም የሀዲያ ልጆች ጋር በጋራ አካባቢው ከምባታ አውራጃ መባሉን በመቃወምና ስሙ ከሀዲያ ህዝብ ማንነትና ጥንታዊ ታሪክ ጋር ፈጽሞ እንደማይገናኝ በመግለጽ በዘመኑ እስከ ነበረው ፖርላማ ድረስ ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል፡፡ በዚህ ተገቢ ባልሆነ የህዝብ መጠሪያ ተቃውሞ ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ከነበራቸው የሀዲያ ልጆች መካከል እነ አቶ ግዛው ገብረጊዮርጊስ፣ አቶ ሀይሌ ቡባሞ አርፊጮ፣ ዶ/ር ሀይሌ ወ/ ሚካኤል፣ አቶ ኤርሳ አዳዳ፣አቶ አሰሙ ወ/ሃና፣ አቶ አበበ ቡሼሮ፣ አቶ ዳዕሞ አበቦ፤ አቶ ኤፍሬም ኦኮሼ፣ አድል ለማጌ፣ አስማች ኑሬቦና ሌሎችንም ገራድ ወልደጊዮርጊስ ቂንጣሞ እራሳቸዉም የጉዳዩ አካል የነበሩት ያስታውሳሉ፡፡

በዚህ የማንነት ትግል ወቅት በሀዲያ ውስጥ የነበሩ የፕሮቴስታንት ቤተ እምነቶች በተለያዩ መልኮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ በዘመኑ የነበሩት ሽማግሌዎች ያስታውሳሉ፡፡

በጉዳዩ ላይ የሚገኙት በርካታ የጽሁፍ መረጃዎችም አካባቢው ወደ ጥንታዊ መጠሪያ መመለሱን የሚያረጋግጡ ካለመሆናቸውም በተጨማሪ ተስፋዬ (1993፣231) አካባቢው ወደ ጥንታዊ መጠሪያ መመለሱን አወሱ ብሎ የጠቀሳቸዉን የሀዲያ ሽማግሌ አቋም በተቃራኒው የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡

እላይ ከተጠቀሰዉ የአካባቢዉ መጠሪያ ወደ ከምባታ አዉራጃነት ከተለወጠበት ዘመን ጀምሮ የሀዲያ ባላባቶች፣ ምሁራን፣ ነጋዴዎችና የአካባቢው ሽማግሌዎች የአካባቢውን አስተዳደራዊ መጠሪያ በመቃወም ያደርጓቸው የነበሩት እንቅስቃሴዎች እንደ አገር ክህደት፣ ዘር የማጥፋት ዕቅድና፣ የጎሣ ጦርነት ቅስቀሳ ተደርገው በከባድ ወንጀልነት በመውሰድ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በሀዲያ ውስጥ የነበሩት ነፍጠኞችና ሌሎችም ጉዳዩ ያልጣማቸው ወገኖች ከፍተኛ ክስ ያቀርቡ ነበረ፡፡ ለምሳሌ፣ ኅዳር 18 ቀን 1963 ዓ.ም. እ.ኢ.አ. የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት ባገር ግዛት ሚኒስቴር የህዝብ ጸጥታ ጥበቃ ለፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ አዲስ አበባ፣ የሀዲያ ባላባቶች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የከባድ ወንጀል ዕቅድ መሆኑን በመግለፅ በሀዲያ የአማራ ክፍለ ህዝብ ነን የሚሉ ሰዎች ያቀረቡትን ማመልከቻ አራት ገፅ አባሪ[29] በማድረግ ፖሊስ ጥብቅ ክትትል እንዲያደርግ ደብዳቤ ተፅፎ ነበረ፡፡ አባሪ በተደረገውም ባለ አራት ገፅ ክስ ውስጥ ከሚገኙት በርካታ ጉዳዮች መካከል የሚከተለው ሀሳብ የዘመኑን ትግልና የትግሉን ተሳታፊዎች ሊገልፅ ይችላል፡፡

[29] ሙሉዉን ደብዳቤ በአባሪ አራት ይመልከቱ፡፡





*9/ ... ከምባታና የጉዴላን ጎሣ ለማጋጨት እኛ ጉዴላ እየተባልን ልንጠራ አይገባም በታሪክ የጉዴላ ነገድ ሀዲያ ነው የሚባለው ስለዚህ የአውራጃውም ግዛት መጠሪያ በከምባታ መሆኑ ቀርቶ የሀዲያ አውራጃ ግዛት እንዲባል እናስደርግ ብለው ... በዚህ ምክንያት በከምባቶችና በጉዴላ ጎሣዎች መካከል ከፍ ያለ የጎሣ ልዩነት ሆኖ በጸብ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተለይም አዲስአበባ የሚገኙ የጉዴላ ጎሣዎች ጉዴላ የሚባል ስማቸውን ሀዲያ ለማሰኘት በቀኛዝማች ሰዩም አኖሬ፣ በአቶ ኃይሌ አርፍጮ፣ በአቶ ግዛው ገብረጊዮርጊስ፣ በአቶ ኤርሣ ዳዳ፣ በአቶ ከበደ ደርጢቦ በተባሉና በሌሎች አማካይነት በየሣምንቱ ቅዳሜ ብርሃንህ ዛሬ ነው ትምህርት ቤት ውስጥ ከፍ ያለ ስብሰባ እያደረጉ ከሚሰበሰቡትም ውስጥ አቶ ኃይሌ ወ/ሚካኤል የዩኒቨርሲቲው መምህርና አቶ ኃይሌ አርፍጮ የተባሉ ሀዲያ በመባል በኢትዮጵያ የሚጠራው ጎሣ ትልቅ ታሪክ ያለው የንጉሥ ዘር ነው ከማንኛውም ጎሣ ይበልጣል በኢትዮጵያ የሚበዘውም ጎሣ ሀዲያ ለመሆኑ የጀርመንና የእንግሊዝ ታሪክ ፀሐፊዎች ፅፈውታል እያሉ ከመሰበካቸውም አልፈው አገር ቤት ድረስ እየሄዱ ሕዝብ እየሰበሰቡ ሲሰብኩ ተከታታይ አልተደረገባቸውም፡፡ ይህን የመሰለ የዘር ልዩነት ማድረግ ባለፈው የሜጫና የቱለማን ዓላማ የተከተለ ስለሆነ መንግሥት በብርቱ ሊያስብበት የሚገባ ነበረ፣ ነገር ግን ለምን ቸል እንደተባለ ስላልገባን ማሳሰብ ግድ ሆነብን...*

እላይ ከክሱ የተወሰደው ሀሳብ፣ የሀዲያ ህዝብ በነፍጠኞች የተሰጠውን የንቀት ስም ብቻ ሳይሆን የአስተዳደር አካባቢውን መጠሪያም ከላይ በከፍተኛ ሁኔታ በተወነጀሉ የሀዲያ ልጆች ግንባር ቀደምነት ይታገል እንደነበረ የሚያስረዳ ነው፡፡ ሆኖም ግን ከሳሾች በሀዲያ ውስጥ የሚኖሩ የአማራ ክፍል ህዝቦች ነን የሚሉት የሀዲያ ህዝብ ከምሁራን፣ ከነጋዴዎች፣ ከባላባቶችና ከአገር ሽማግሌዎች በተውጣጡ ተወካዮች

አማካይነት የአስተዳደር አካባቢ ስያሜን በተመለከተ የነበራቸውን ጥያቄ በክስ ማመልከቻቸው ውስጥ በተሳሳተ መንገድ ነበረ የገለጹት። በሌላ አነጋገር፣ የሀዲያ ህዝብ የአስተዳደር አካባቢ ስያሜ በተመለከተ ያቀርብ የነበረው ጥያቄ "የአውራጃ ግዛት መጠሪያ በከምባታ መሆኑ ቀርቶ በሀዲያ አውራጃ ግዛት እንዲባል" ሳይሆን መጠሪያው የአውራጃውን የህዝብ ብዛትና የጉሳ ስብስብ ያማከለ እንዲሆን ነበረ።

ይህንን የሀዲያ ህዝብ ጥያቄ በተመለከተ ስክቡር የህዝብ ጸጥታ ባለሥልጣን በአድራሻና ለአገር ግዛት ሚኒስቴር፣ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴና ለፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ በግልባጭ ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤል[30] እና አቶ ኃይሌ አርፍጮ የአማራው ክፍል ህዝብ ነን በሚሉት፣ ነገር ግን ስምና ፊርማቸው በማመልከቻቸው ውስጥ በልተካተተ ሰዎች፣ ለተነሳባቸው ክስ በሰጡት መልስና የመልስ ሰጭዎቹ ፊርማ በሰፈረበት ደብዳቤ[31] አራተኛ ተራ ቁጥር የሚከተለውን ሀሳብ እናገኛለን።

[30] ዶክተር ኃይሌ ወልደሚካኤል በህይወት ዘመናቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ ካበረከቷቸዉ ተላላቅ አስተዋጽኦዎች መካከል በ1960ዎቹ እ.ኢ.አ. በኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ ፈታኝ በሆነ ወቅት የኢትዮጵያ መምህራን መህበር ሊቀመንበር፣ የእድገት በህብረት ዘመቻ ዋና ጽህፈት ቤት የፕሮግራሞች አስተባባሪ፣ ከ1969 - 1971 እ.ኢ.አ. የባህል ሚኒስትር፣ በብሄረሰቦች እንስትቲዩት የማህበራዊ ዘርፍ ሃላፊ፣ ከ1980 በኋላ በመንግስት ምክር ቤት በሚኒስትር ማእረግ የአስተዳደር ዘርፍ ሃላፊ፣ በኢህአዴግ ስልጣን ዘመን የሽግግር መንግስት የህዝብ ተወካዬች ምክር ቤት አባል፣ከ1993 ዓ. ም. እ.ኢ.አ ጀምሮ የአፍሪካ ቤዛ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት፣በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰርና ከ40 በላይ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችን ያሳተሙ፣ አብሮነት በኢትዮጵያ የሚል መጽሃፍ ጸሃፊና ሌሎች በርካታ የኢትዮጵያንና የትዉልድ አካባቢያቸዉን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን ያነገቡ አደረጃጀቶችን በሃላፍነት የመሩ ታላቅ ሰዉ ነበሩ።

[31] ደብዳቤዉን በአባሪ አምስት ይመልከቱ።





*4/...በአውራጃው ከሚገኝ ህዝብ ሶስት አራተኛ የሚሆነው የሀዲያ ህዝብ በሌላ አውራጃዎች ለምሳሌ፣ ተጉለትና ቡልጋ ጨቦና ጉራጌ ወዘተ. እንደተደረገ ሁሉ የከምባታም አውራጃ የሀዲያና የከምባታ አውራጃ ይባልልን ብሉ ህዝቡ ያመለከተውን ምክንያት በማድረግ ባገሩ ሰላም የጠፋ አስመስሉ ህዝቡን ለማሳጣት የተደረገ ነው።*

በመሆኑም የሀዲያ ህዝብ ጥያቄ የነበረው የአስተዳደር አካባቢው መጠሪያ የሀዲያና የከምባታ አውራጃ እንዲባል እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህ ጥያቄ የሀዲያ ህዝብ ለሌሎች ህዝቦች ማንነትም ጭምር ምን ያክል ጥንቀቅ እንደነበረ የሚያስረዳ ነው። በጥያቄያቸው እንዲስተካከል ያቀረቡት አዲስ የአስተዳደር አካባቢ መጠሪያ የብሄሮች ስም ቅደም ተከተል ሁለቱም ብሄሮች ያላቸውን የህዝብ ብዛት ልዩነት ብቻ አመላካች እንደነበረ በዘመኑ በጉዳዩ ተሳታፊ የነበሩ የሀዲያ ሽማግሌዎች ያስረዳሉ። በመሆኑም ስሙ የተለወጠበት ዘመንና የተለወጠበትን ሁኔታን ተስፋዬ /1993/ በተገቢ መንገድ ቢያስረዳም፣ በለዉጡ ላይ ያለው አመለካከትና ማስረጃ በማገኛውም መስፈርት መሰረተ-ቢስ ሆኖ እናገኛዋለን።

ምንም እንኳን ጥቂት የአካባቢዉ ባላባቶች ከጣሊያን ወደ ሀዲያ መምጣት ጋር ተያይዞ ከቀድሞ ገባሮች ጋር በነበራቸው ለሉታዊ ግንኙነት ጊዜያዊ ችግርና ስደት ቢገጥማቸውም፣ በአጠቃለይ የጣሊያን መምጣት በሀዲያ ህዝብ ዘንድ የነፍጠኛዉን ስርአት ለመዋጋት መልካም አጋጣሚ ፈጥሮለት ነበረ። ህዝቡ ለጣሊያን አስተዳደር የነበረውን ጊዜያዊ ድጋፍ ካጠናከሩት መሰረታዊ ምክንያቶች የሚጠቀሰው በወቅቱ

የጣሊያን አስተዳደር ገባርነትን በማስወገድና የግብር ውዝፍን በማስቀረት ጫናን ማቃለል መቻሉ ነበረ። ከዚም በተጨማሪ ግብር በመቀነስ የአካባቢውን ህዝብ ድጋፍ ጠብቆ ለማቆየት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። የገባር ስርአት ሲወገድ የሀዲያ ገበሬዎች የቀድሞ መሬታቸው ባለቤቶች መሆን ችለዋል። ሆኖም ግን የጣሊያን አስተዳደር ለመንገድ ሥራና ለሌሎችም መሠረተ ልማት ግንባታዎች የቀድሞ ገባሮችን ጉልበት መበዝበዙና የተወሰኑትን ደግሞ የጣሊያን ምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር ሠራዊት አካል አድርጐ በመመልመል ማስቀየቱ የአካባቢው ህዝብ በጣሊያን አስተዳደር ላይ የነበረውን እምነት እንዲሸረሽርና ይሰጠው የነበረው ድጋፍ እንዲቀንስ አድርጓል።

በጣሊያን አስተዳደር ለአጭር ጊዜ የቆየው የሀዲያ ገበሬዎች አንጻራዊ ነጻነትና የግብር ሥርዓት መሻሻል በ1940 ዓ.ም. የጣሊያን ፋሽስት መንግሥት ወደ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከመግባት ጋር ተያይዞ ችግር ዉስጥ እየገባ ሄዷል። በግንቦትና ሰኔ 1941 የኢትዮጵያ አርበኞች በእንግሊዝ ወታደሮች ጋር በመተባበር የጣሊያንን አስተዳደር ከሀዲያ አካባቢ በማባረር ሊያስወጡ ችለዋል። በዚህ በጣሊያን ፋሽስት ወታደሮችና የኢትዮጵያ አርበኞች ከእንግሊዞች ጋር ባደረጉት ጣሊያንን ከኢትዮጵያ የማስወጣት ጦርነት ብራዉካምፔር (1980፣ 437) እንደጻፈዉ የሀዲያ ህዝብ እንደ አጠቃላይ ህዝብ በየትኛውም ወገን ሳይሆን በጦርነቱ ሳይሳተፍ ገለልተኝነት መርጧል። ነገር ግን ከሀዲያ ውስጥ የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ከሁለቱ አንደኛውን ወገን በመደገፍ (ጣሊያንን ወይም የኢትዮጵያን አርበኞች) በጦርነቱ ተሳትፈዋል። የኢትዮጵያን አርበኞች በመደገፍ በጊቤ በረሃ ከጣሊያን ጋር ከተዋጉት የሀዲያ ጀግኖች መካከል ገራድ ወልደጊዮርጊስ ቁንጣሞንና ግራዝማች ሀይሌን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል።





ብረውካምፔር (1980፡ 437) እንደገለፀው በዚህ ተመሳሳይ ወቅት በሀዲያ አካባቢ ትልቅ ችግር ሆኖ የነበረው በባዳዋቾ ሀዲያዎችና በወላይታ መካከል ይደረግ የነበረው ጦርነት ነበር። በዚህ ጦርነት ምክንያት የተፈጠረው አለመረጋጋት የጣሊያን አስተዳደር ተወግዶ አፄ ሀይለስላሴ ወደ ሥልጠናቸው ከተመለሱ በኋላም እስከ 1942 ዓ.ም. ድረስ ቀጥሏል።

በአጠቃላይ የጣሊያን አስተዳደር በነበረበት በአምስቱ ዓመታት ከ1936 -1941 እንደማንኛውም የኢትዮጵያ አካባቢዎች በሀዲያ አካባቢም የመንገድና የድልድይ ሥራ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ነገር ግን የጣሊያን መሠረት ካላቸው ሚሲዮናዊያኖችና የውጪ የሃይማኖት ተቋማት በስተቀር ሌሎች በአጠቃላይ በመባረራቸው ቀደም ሲል መስፋፋት ጀምሮ የነበረው የዘመናዊ ትምህርት ሁኔታ በጣሊያን የወረራ ዘመናት የመዳከም አዝማሚያ አሳይቷል።

አፄ ሃይለ ሥላሴ ወደ ሥልጣናቸው ከተመለሱ በኋላና የነፍጠኛ ሥርዓት እንደገና በሀዲያና በሌሎችም የኢትዮጵያ ህዝቦች ሲጫን ከ1941 ጀምሮ ንጉሡ በጣም የተማከለ አስተዳደራቸውንና የመሬት ከበርቴነትን ሥርዓትን ከቀድሞ የበለጠ አጠናክረው ገፍተውበታል።

የሀዲያ ህዝብ የኢትዮጵያን በጣሊያኖች የመሸነፍ አጋጣሚን ለአመፅ መገልገሉን ለመበቀል ዳግም ወደ ሥልጣን የተመለሰው የአፄ ሃይለ ሥላሴ መንግሥት በጣሊያን አስተዳደር ዘመን የቀድሞ የመሬት ይዞታቸውን ከሸዋ ገዥዎች መልሰው በመውሰድ ከገባርነት ነፃ የወጡት የሀዲያ ገበሬዎችና በተለያዩ ወቅቶች ከገባርነት ሸሽተው ከአካባቢው

የተሰደዱ ገባሮች መሬታቸው ተነጥቆ የቤተ መንግሥት መርጃ መሬት እንዲሆን ተወስኗል[32]፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወደ ሥልጣኑ ዳግም የተመለሰው የአፄ ሃይለ ሥላሴ መንግሥት ህዝብ አልሰፈረባቸውም የሚልና ቁርጥራጭ መሬቶች የሚል ስያሜ በመስጠት የሀዲያ ህዝብ እንደ ገብያ ቦታ፣ የግጦሽ መሬት፣ የቀብር ቦታ፣ የጋራ መሰብሰቢያና የመሳሰሉት ማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ መሬቶችን ጠፍ መሬት በማለት ወርሷል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ዘላቂ ትርጉም ካላቸው ቅጣቶች በተጨማሪ ከሀዲያ ህዝብ ገበሬዎች በበርካታ ሺህ የሚቆጠር ከብት በቅጣት መልክ ደግሞ ወደ ሥልጣን በተመለሰው የአፄ ሀይለስላሴ መንግሥት ተወርሷል፡፡ አብዛኞቹ የሀዲያ ገበሬዎች በሚደርስባቸው ዘርፈ-ብዙ ጫና በገባርነት የያዙት መሬት በመሸጥ በራሳቸው መሬት ላይ ወደ ጭሰኝነት ተሰውጠዋል[33]፡፡

[32]ይህንን ሁኔታ ላጵሶ (1982፤ 98-99) ሲገልፅ በጠለት ወረራ ወቅት የአገሩ የጉልተኛዉ መደብ መሪዎችና አባሎች ከንጉሳቸዉ ጋሪ ከአገሩ በሸሸት ከወጡ በሁዋላ የአዉራጃዉ ህዝብ ሆሳዕናን አቃጥሎ ... በጉልተኛ ተይዞበት የነበረዉን መሬት አለምንም ድርድርና ገደብ መልሶ እንደወሰደ.....፡፡ ይህንን እርምጃ... እንደ ታላቅ ወንጀል በመቁጠር በድህረ ጦርነት የጉልተኛዉ መንግስት ጠፍ መሬት ነዉ በሚል ሽፋን በመንግስታዊ በቀል... የሀዲያን ህዝብ መሬት መዉሰድ ጀመረ፡፡ ይህ ከህዝብ የተወሰደ መሬት ለመንግስት ባለስልጣኖችና ሹማምንት... የንጉስ ባለዉለታዎች ናቸዉ ተብለዉ በደሃ መሬትና ገንዘብ ለሚሸለሙ ጉልተኞች በስጦታ እንዲሰጣቸዉ የቤተ-መንግስት መርጃ መሬት በሚል ስሪትና ፅሀፈት ቤት ሥር እንዲያዝ ከንጉሱ ልዩ ትዕዛዝ ተሰጠ፡፡

[33] በሸዋዉ ጪቄኝ ፊዉዳላዊ ሰርአት ዘመን ገባር ማለት ባለመሬት ሲሆን ጢሰኛዉ ግን በፊዉላዊ ስምምነት የሰዉን መሬት እያረሰ የሚኖር የግል መሬት የሌለዉ አርሶ አደር ነዉ (ላጵሶ 1982፣ 35) ፡፡





በአጠቃላይ ከ1941 ጀምሮ እስከ ንጉሣዊው ሥርዓት ውድቀት ድረስ ባሉት ዓመታት ከቤተ መንግሥት መረጃ መሬት ውስጥ በስጦታ በሀዲያ ህዝብ ውስጥ መሬት የተሰጣቸው ነፍጠኞች ሁኔታዎችን ለሀዲያ ገበሬዎች የከፋ በማድረግ መሬት የገዙ ግለሰቦች የአካባቢውን ህዝብ በጭካኔ በመበዝበዝ ህይወታቸውን ወደ ጭሰኝነት ቀይረዋል፡፡ በአካባቢው የነበረው ብዝበዛና ጭቆና ያስመረራቸው የሀዲያ ልጆች በየበረሃው አዲስ በተከፈቱና ከፍተኛ ጉልበትና የህይወት መስዋዕትነት በሚጠይቁ አደገኛ በሆኑ የእርሻ ልማቶች በወዛደርነት ለማገልገል ተሰደዋል[34]፡፡ በዚህ አንፃር በዋናነት የሚጠቀሱት የወንጂና የመታሃራ ስኳር ፋብሪካዎች ናቸው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በንጉስ ኃይለስላሴ ዘመን እንደሌሎችም የደቡብ አካባቢዎች የሀዲያ መሬት በተለያዩ ስያሜዎች ለጉልተኞች፣ ለሸዋ ገዥዎችና የአካባቢው ባላባቶች እንዲሁም ለአንዳንድ የአካባቢው ቤተሰቦች የተከፋፈለ ነበረ፡፡ የተወሰነው የሀዲያ መሬት የግምት መሬት ተብሎ ሲጠራ ይህ በውርስ መብት የሚያዝ መሬት ነው፡፡ በመሆኑም ባለቤቱ መሬቱን ለልጆቹ የማውረስ መብት አለው፡፡ በግምት መሬት ላይ የሚኖሩ ግለሰቦች ምንም እንኳን ማንኛውም የጉልበት አገልግሎት ለነፍጠኞችና ለባላባት የመስጠት ግዴታ ቢጣልባቸውም ከሚሰሩበት መሬት ግን አይነቀሉም፡፡ ምክንያቱም ግለሰቦቹ በህግ የተመዘገቡ ጭሰኞች ናቸው፡፡ ለመሬታቸውም በቀጥታ ለመንግስት ግብር እንደሚከፍሉ ብራውከምፔር እና ጥላሁን (1999፡ 63) ይገልጻሉ፡፡

[34] በወንጂ፣ በሸዋና በመተሃራ የስኳር ፋብሪካዎች ከሚሰሩ ወዛደሮች መካከል ምናልባትም 90% የሀዲያና የከምባታ ተወላጆች መሆናቸዉ ሀቅ ነዉ፡፡ በዚህ አኳያ ከአካባቢዉ በ1950ዎቹ ዓመታት የወባ ትንኝ እስኪጠፋ ድረስ ከ1946 ጀምሮ በአዋሽ ሸለቆ በወባ በሽታ ያለቀዉን የሀዲያና የከምባታ ህዝብ ...በብዙ ሽህ ...መገመት ይቻላል (ላዲሶ 1982፣ 103) ፡፡

ሌላው የመሬት ዓይነት የጋሻ መሬት የሚባል ሲሆን ይህ የተለካ መሬትን ያመላክታል። የጋሻ መሬት የሚሰጣቸው ግለሰቦች ለፊውዳሉ መንግስት ገዥዎች በቀጥታ ግብር እየከፈሉ መሬቱን ይጠቀማሉ። በጋሻ መሬት የሚሰሩ ጭሰኞች ከሚሰሩበት መሬት በባለጋሻው ሊነቀሉ ይችላሉ። የተቀረው በግለሰቦች የተያዘ መሬት የኩዳድ መሬት እና የማደሪያ መሬት ተብለው ይመደባሉ። የኩዳድ መሬት በመልከኞች የተያዘ ሲሆን ሰፋፊ የእርሻ ልማት ስራዎች በጭሰኞች ጉልበት ወይም በሌሎች ዘመናዊ መሳሪያዎች የሚካሄድበት ናቸዉ። የማደሪያ መሬት የሚባለዉ፣ በጡረታ ወይም በደመወዝ ምትክ መንግስትን ላገለገሉ ወይም ለሚያገለግሉ የሚሰጥ መሬት ሆኖ የመሬቱ ተጠቃሚ መሬቱን ለልጅ የማውረስ መብት አይኖረውም። ተጠቃሚው ለማደሪያ መሬት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

የሀዲያ መሬት በንጉሱ ከፍተኛ ባለስልጣናት በስፋት ተይዞ እንደነበረ የሀዲያ ሽማግሌዎችና የጽሁፍ ማስረጃዎች ያወሳሉ (ጌዲዎን 2008፡32) ። ለምሳሌ ፣ ራስ ጌታቸው አባተ /የአባተ ቧያለው ልጅ/ በባዳዋቾ ብቻ ከ80 ጋሻ መሬት በላይ ባለቤት ሲሆን ደጃዝማች አንበርብር ከ60 ጋሻ መሬት በላይ በተመሳሳይ አካባቢ ይዘው ነበረ።

እነዚህ ሰፋፊ የሀዲያ መሬቶችን የያዙ ገዥዎች ሀብታቸውን በአግባቡ ለመቆጣጠርና ለመከታተል እንዲሁም ለተለያዩ ምርቶቻቸው በአቅራቢያ ገበያ ለመፍጠር አነስተኛ ከተማዎችንና የገበያ ቦታዎች መስርተዋል። ለምሳሌ፣ በባዳዋቾ በጣም ሠፊ ጋሻ[35] መሬት የነበራቸው ራስ ጌታቸው አባተ የሾኔን /Shone/ ከተማ እንደመሰረቱ ይነገራል።

[35] ጋሻ፣ በንጉሳዊዉ ስርአት ለነፍጠኞች የሚሰጥ መሬት ሲሆን አንድ ጋሻ መሬት በግምት 40 ሄክታር ይሆናል (ብራዉካምፔር 1999፡ 57)።





ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ መሬታቸው ተነጥቆ አስከፊ የሆነ የጭሰኝነት ህይወት እንዲመሩ የተገደዱት የሀዲያ ገበሬዎች የተወሰኑት ከቀያቸው በመሰደድ ለከፋ የጉልበት ብዝበዛ በተለያዩ የእርሻ ልማቶችና ኢንዱስትሪዎች በወዛደርነት ለመቀጠር ቢጋለጡም የተቀሩት በድፍረት ጭቆናውን በራሳቸው ትውልድ አካባቢዎች ተቃውመዋል።

የሀዲያ ገበሬዎች በጨቋኙ የጉልተኛ ሰርአት ላይ ካካሄዱት ጠንካራ አመጾች[36] በዋናነት የሚጠቀሰው በባደዋቾ የጃርሶ /Jaarso/ ገበሬዎች አመጽ ነው። የባደዋቾ መሬት ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዋና ዋናዎቹ የፊውዳሉ መንግሥት ገዥዎች እጅ የተያዘ የጋሻ መሬት የበዛበት ነበረ። በመሆኑም የጭሰኝነት ሰቆቃ እጅግ የከፋ ነበረ። በመሆኑም በ1946 ዓ.ም. የጃርሶ /Jaarso/ ገበሬዎች በጨቋኙ ስርአት ላይ አምጸዋል[37]። የጃርሶ ገበሬዎች በአመጽ ወቅት ያነሷቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ግብር እንዲቀነስና መሬት ለገበሬው እንዲመለስ ነበረ። እነዚህ ስር ነቀል የስርአት ለውጥን በውስጣቸው ያነገቡ የጀርሶ ገበሬዎች በአመጽ የተደገፉ ጥያቄዎች በጨቋኙ የፊውዳል መንግስት ላይ መታሰባቸው በራሱ እጅግ አደገኛ ተብለው የሚወሰድበት ወቅት ነበረ።

ይህንን በጣም ጠንካራና የተቀነባበረ የገበሬዎች አመጽ የመሩት የአካባቢ ገበሬ የነበሩና በኋላ የግራዝማችነት ማእረግ ያገኙት ሰጋሮ ባንቴ /Saggaaro Baante/ ናቸው። ግራዝማች ሰጋሮ ባንቴ /Saggaaro Baante/ የገበሬዎችን ጦር በማደራጀት

[36] ላጵሶ (1982፡ 97) የሀዲያ የገበሬ አመጽ ምንጮች መሬትና ግብር እንደሆኑ ይገልጻል።

[37] የጃርሶ ገበሬዎች አመጽ ከቀዳማዊ የወያኔ አመጽ (1943) ተከትሎ የተከሰተ ሲሆን ለረጅም አመታት ያለመፍትሄ የዘለቀ አመጽ ነዉ።

አካባቢው ለፊውዳል ገዥ መደብ ፈጽሞ የማይመችና እጅግ የሚያሰጋ እንዲሆን በማድረግ፣ ከፍተኛ የሆኑ የመንግሥት ተሿሚዎችን በማስፈራራትና በአቅማቸው መመለስ የማይችሉና ለንጉስ ነገስቱም ቢያቀርቡ እጅግ አስደንጋጭ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳሳት ለአካባቢው ገዥዎች ትልቅ የራስ ምታት ሊሆኑ ችለዋል፡፡ አመጹን በመምራት ላይ እያሉ ግራዝማች ስጋሮ ባንቴ በመንግስት ሀይሎች ተይዘው አዲስ አበባ ላይ ለረጅም ጊዜ ታስረው ቆይተዋል፡፡

ግራዝማች ስገሮ በእስር ከአካባቢው ሲወሰዱ የገበሬዎቹ አመጽ የበለጠ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ አመጹ የበለጠ ተባብሶ እንዲቀጥልና አዳዲስ የትግል ሥልቶችን ጥቅም ላይ እንዲዉል በማድረግ ከግራዝማች ስጋሮ ባንቴ መታሰር በኂላ አመጹን መምራት የቀጠሉት በሊሎ ወንጬሶ /Balliillo Wonceesso/ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ በሊሎ ወንጬሶ ወይም በቅጽል ስማቸው አባቴራ/Abbaataara/ ተዋጊ ገበሬዎችን በማደራጀት አመጹን ወደ ጦርነት ቀይረውታል፡፡ ከዚሀም በተጨማሪ አባታራ የባደዋቾን ገበሬዎች ግብር እንዳይከፍሉ በማድረግ ግጭቱ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲሸጋገር አድርገዋል፡፡

የአባቴራ እርምጃዎች ለፊውዳሉ ጨቋኝ መንግሥት በጣም አስጊ እየሆኑ በመሄዳቸው የንጉስ ነገስቱ መንግስት የተለያዩ ዘዴዎችን አጣምሮ በመጠቀም አመጹን የማስቆም እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ መንግስት አመጹን ለማስቆም ከተጠቀማቸው ዘዴዎች አንዱ የነበረው ለሀዲያ ባላባቶች የተሻለ ጥቅማ ጥቅም በመስጠት ከጐኑ እንዲሰለፉ በማድረግ የባላባቶችን ታማኝነትና የመንግስት አቋም ደጋፊነት ማረጋገጥ ነበረ፡፡ በዚህ መልኩ መንግስት ከቀረባቸው የሀዲያ ባላባቶች መካከል





እነ ፊታውራሪ ጌጃ ገሪቦ፣ ቀኝአዝማች ሉዱቦ ቡኑሼና ቀኝአዝማች ስዩም አኖሬ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

የሀዲያ ባለባቶችን ድጋፍ ያገኘው የፊውዳሉ መንግሥት በጃርሶ አካባቢ የባደዋቾ ሀዲያ ገበሬዎች ላይ በ1962 ዓ.ም. ወታደራዊ እርምጃ በመውሰድ በአካባቢው ገበሬዎች ላይ አስከፊ የሆነ ግፍ ፈጽሟል፡፡ በመጨረሻም በ1969 ዓ.ም. የአመጹ መሪ የነበረውን ባሊሎ ወንጬሶን ወይንም አባቴራን በማሰር የጀርሶ ገበሬዎችን እመፅ ማርገብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የአጼ ሀይለ ስላሴ መንግስት ወደ ሥልጣን ከተመለሰ በኂላ እስከ 1960 ዓ.ም. ድረስ የሀዲያ ህዝብ በከምባታ አውራጃ ውስጥ በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ሥር እንዲተዳደር ተደርጓል፡፡ ከዚያም እስከ ንጉሳዊ ስርአት ውድቀትና በደርግ ስርአትም ለተወሰኑ ዓመታት በተመሳሳይ የአውራጃ መጠሪያ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ስርአት ስር እንዲተዳደር ተደርጓል፡፡

ከ1941 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1974 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ሰላሳ ሶስት አመታት ውስጥ የከምባታን አውራጃ (የሀዲያ ህዝብ በአጠቃላይ በዚሁ አውራጃ ውስጥ የተጠቃለለ መሆኑ ይታወሳል) እንድም የአካባቢው ተወላጅ አስተዳድሮት የማያውቅ ሲሆን፣ ከላይ በተጠቀሰው ረጅም ዘመን የጉልተኞችን መብትና ጥቅም እንዲሁም የነፍጠኛውን ስርአት ፍላጐት እንዲያስጠብቁ የአካባቢው ገዥዎች የተሾሙት በሸዋ መንግስት እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ከ1941-1974 ዓ.ም. ባሉት የሰላሳ ሶስት ዓመታት ጊዜ 14 ገዥዎች በአውራጃው ተሹመው የነፍጠኛውን ሥርዓት አገልግለዋል፡፡ እነዚህም

ግስሰቦች ራስ አደፍርስ ናደው፣ ደጃዝማች ዳምጠው መሸሻ፣ ፊታውራሪ ክፍሌ ዳዲ፣ ፊታውራሪ ተሰፋዬ እንቁስላሴ፣ ደጃዝማች ሽፈራው ወንድም አገኘሁ፣ ደጃዝማች ዘለቀ ደስታ፣ ደጃዝማች ሽፈራው ወንድም አገኘሁ (ለሁለተኛ ጊዜ)፣ ፊታውራሪ ካሳ ኪዳነ ማርያም፣ በጅሮንድ ዘውዴ ሙላት፣ ደጃዝማች ዮሀንስ ግርማይ፣ ደጃዝማች ዘውዴ ጥላሁን፣ ፊታውራሪ ሩጋ አሻሜ እና ፊታውራሪ ተድላ ታምራት በቅደም ተከተል ናቸው። እላይ በተጠቀሰው የሰላሳ ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ፣ ከአጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ ውስጥ ቀኛዝማች ስዩም አኖሬ ብቻ የወረዳ ገዥነት ሹመት ተሰጥቷቸው የሶሮ ወረዳ አስተዳደር ተደርገው አገልግለዋል። በዘመኑ ቀኛዝማች ስዩም ያስተዳድሩ የነበረው ወረዳ ዶንጋና ጥንባሮ ይባል የነበረ ሲሆን፣ ሶሮ ወረዳ የሚል በከምባታ አውራጃ ያልተሰመደና የሌለ መጠሪያ ይጠቀማሉ በሚል ቀኛዝማች ስዩምን፣ ቀዲዳ ጋሜላ የሚሰውን ወረዳ ባዳዋቾ ይላሉ በሚል የሕግ ጠበቃ የሆኑት አቶ አበበ ቡሼሮን፣ የጉማ አድማ እየጠነሰሱ ይገኛሉ ተብለው ታህሳስ ሰባት 1963 ኢ.ኢ.አ. ሰሸዋ ጠቅላይ ግዛት ጽህፈት ቤት አባሪ[38] ቡተደረገው ደብዳቤ ተከሰው ነበረ።

## 2.7. የሀዲያ ፖለቲካዊ ስርአት ግምገማ

የተሰያዩ የክርስቲያኑ መንግስት ዜና መዋዕሎች፣ የአረብ ጸሀፊዎች እና አውሮፖዊያን የሀዲያን ጥንታዊ የአስተዳደር ዓይነትን ንጉሳዊ ስርዓት እንደሆነ ይገልፃሉ። ነገር ግን የሀዲያን ህዝብ የዛሬው ባህላዊ የአስተዳደር አወቃቀር፣ የአፈ ታሪክና የጽሁፍ ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት በሀዲያ ህዝብ ታሪክ አንድ ማዕከላዊና ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን የተሰጠው የአስተዳደር ዓይነትን እንደነበረዉ አያሳይም።

[38] ሙሉዉን ማመልከቻ በአባሪ ስድስት ይመልከቱ።





ብራውካምፔር (1973: 46) እንደሚገልጸው የሀዲያ ህዝብ ንጉሳዊ አስተዳደር እንደነበረው የሚገልጹት አብዛኞቹ የራሳቸውን ማህበረሰብ የአስተዳደር ስርአት አረዳድን ትክክል ባልሆነና በመረጃ ባልተደገፈ ሁኔታ ወደ ህዲያ በማስፋፋት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የሰሜኑ የክርስቲያን መንግስት የዜና መዋዕል ጸሀፊዎች ናቸው። እነዚህ ፀሐፊዎች የሀዲያን ገራዶች /Garadduwwa/ የራሳቸውን ማህበረሰብ አረዳድ በማስፋፋት ንጉሶች እንደሆኑ ጽፈዋል[39]። ከዚህም በተጨማሪ የዜና መዋዕል ጸሀፊዎች ለህዲያ ገራዶች ተጨማሪ የክርስቲያኑን መንግሥት ማእረግ ሲጨምሩ መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ፣ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ (1968: 97) አፄ ሠርጸ ድንግል ወደ ደቡብ ያደረጉትን ጦርነቶች ሲገልጽ ስለ ሀዲያ ህዝብ የሚከተለውን ጽፏል።

> *የሸዋም ሕዝብ ከሀዲያ ሕዝብ በቀር ገባላቸው። የሀድያ ህዝብ ግን ደብልጡ እስላም ስለነበረ ባላባቱን አፄ ገራድን ይዞ ተዋጋቸው። ይኸም ባለባት ከዚህም ቀደም ንጉሡ የሾሙትን ሮም ሰገድን የገደለ ነው።*

ይህ መረጃ ከዘመኑ የነገስታት የእለት ውሎ መዝጋቢዎች የተገኘ ሲሆን በዘመኑ የሀዲያ ህዝብ ባላባት እና አጼ የሚባሰዉን ማእረግ ሰራሱ መሪዎች የማይጠቀምበት ወቅት ነበረ። ከዚህ በተጨማሪ በሀዲያ ገራድ የማእረግ ዓይነት ሲሆን ከላይ በተጠቀሰው ጽሁፍ ግን እንደ ግለሰብ ስም ጥቅም ላይ ውሏል። በመሆኑም የህዝብን መሪዎች ትክክለኛ ማእረጋቸውን እንደስማቸው በመውሰድ ጸሀፊዎቹ

[39] ተክለጻድቅ መኩሪያ (1993: 431) ንጉስ ስለተባለዉ ሁኔታ ሲገልጽ የሀዲያዉን ባለባት ያምደጽዮን የጦርነት ታሪክ ጸሀፊ የሀዲያ ንጉስ ሲለዉ የቀረዉ ሁሉ… የሀዲያ ገራድ ነዉ የሚለዉ ብሎ ጽፏል።

የክርስቲያኑን መንግስት ማእረጐች የሆኑትን እንደ ባሰባት እና አጼ በመጨመር የሀዲያን ህዝብ አስተዳደራዊ ስርአት ትክክለኛ ባልሆነ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል ክፍተት ሲፈጥሩ መመልከት ይቻላል። የዘመኑን ዜና መዋዕል ጸሀፊዎች ለህዝቦች መሪዎች ከሚሰጡት ማእረግ በመነሳት መረዳት እንደሚቻለው፣ በእነርሱ አረዳድ ህዝብ ያለ ንጉሥ ፈላጭ ቆራጭና የተማከለ አስተዳደር ሲኖር እንደማይችል አድርገው እንደሚቆጥሩ መገንዘብ አያዳግትም።

በሀዲያ ጥንታዊ የአስተዳደር ስርዓት ገራድ /Garaad/ ትልቁ ማዕረግ ሲሆን፣ የገራድነት ስልጣን ግን ፈላጭ ቆራጭና የተማከለ እንዳልሆነ የሀዲያ ህዝብ የአፈ ታሪክ ማስረጃዎችና ሌሎችም የጽሁፍ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ።

ከዚህ አንጻር በብራውክምፔር (1973፡ 46) ላይ እንደሰፈረውና የሀዲያ አጠቃላይ ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታ እንደሚያስረዳው ገራድ /Garaad/ በአንጻራዊነት እኩል ቦታ በሚሰጣቸውና ተመሳሳይ መብትና የኑሮ ሁኔታ በሚጋሩ የሀዲያ ከብት አርቢ ህዝብ መካከል የመሪነት ሚና እንዲጫወት የሚያስችለውን ስልጣን በህዝብ ስምምነት ያገኘ ነገር ግን ፍጽማዊ ስልጣን የሌለው ባለማእረግ ነው። የገራዳነትን ማእረግ በመያዝ ከላይ እንደተጠቀሰው የህዝብ መሪ ለመሆን መሰረታዊ መመዘኛው የግለሰቡ ብቃት ነው። ለምሳሌ በሀዲያ ታሪክና ባህል መሰረት የብቃት አመልካቾች ከሚባሉት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የግለሰቡ ህዝብን አስተባብሮና አቅፎ የመምራት ችሎታ፣ በህዝብ ውስጥ ወይም በሀዲያና በሌሎች ህዝቦች መካከል የሚከሰቱትን የተለያዩ ችግሮችን የመመርመር፣ የመተንተንና ውጤታቸውን የመተንበይ የአእምሮ ብቃት፣ የሀዲያ ህዝብ ያለፈውን አጠቃላይ ታሪክና ልምድ ጠንቅቆ





ጠንቅቆ የማወቅ ችሎታ፣ የህዝብን አኃምሮና አስተሳሰብ ሊያሳምን የሚችል የንግግር ችሎታ፣ ሀቀኝነትና ጀግንነት፣ ምሳሌ ሊሆን የሚችል የስራ ትጋትና ሀብት እንዲሁም ጽኑ የህዝብ ፍቅር ናቸው።

ይህ በሀዲያ ታሪክና ባህል ትልቅ የሆነው የገራዳነት ሥልጣን ከአባት ወደ ልጅ እንደመብት የሚተላለፍ ሳይሆን በህዝቡ እምነት ልጅ አባቱ ያሟላውን የገራዳነት መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ይገለጻል። አባት ሲሞት ወይም በበሽታና እርጅና አቅሙ ሲደክም ከወለዳቸው ልጆች መካከል ሀላፊነቱን የሚሸከም ካልተገኘ የሀዲያ ህዝብ ሌላ ጠንካራና ተገቢውን መስፈርት የሚያሟላ መሪ የመምረጥ መብት አለው። በመሆኑም በሀዲያ ታሪክና ባህል ቀጣይ ገራድ በሚታሰብበት ወቅት አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ከስምምነት መደረስ አለበት። ይኸውም:-

| | |
|---|---|
| ቤት አና ለቦሆንኄ? | "ልጅ የአባት ዓይነት የመሪነት |
| Beet anna labohonnihee? | ችሎታ አለው ወይ?" |

እላይ የተጠቀሰው ጥያቄ መልስ በሀዲያ ባህል ቀጣዩን መሪ ይወስናል።

የሀዲያ ህዝብ በታሪኩ ካሳለፋቸው ረጅም የጦርነትና የማንነት ትግል አንጻር አብዛኞቹ የሀዲያ ገራዶች በህዝብ የተመረጡ / elected/ የጦር መሪዎች ነበሩ። እነዚህ የሀዲያ ገራዶች ገጥአና / Gaaxxanna/ ወይም አበጋዝ /Abagaaz/ ሲሆኑ በማንኛውም ጉዳይ (በሰላማዊ ሆነ ሌላ)፣ በሌሎች ህዝቦች ዘንድ የሀዲያን ህዝብ የሚወክሉ ሆነው ያገለግላሉ። በመሆኑም የገራዳነት

ስልጣን በህዝብ ከታች ወደ ላይ የሚሰጥ ስልጣን ሆኖ ህዝቡን በጦርነትም ሆነ በሰላም የመወከልን ግዴታ የያዘ ነው።

በሀዲያ ታሪክና ባህል መሰረት ከላይ ከተጠቀሰው የህዝብ ተወካይነት ሥልጣን በተጨማሪ የሚታወቀው ሌላው ከፍተኛ ስልጣን አንጃንቾ /Anjaancho/ ተብሎ የሚታወቀው መንፈሳዊ ሥልጣን ነው። አንጃመኖ /Anjaammano/፣ በሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓትና በመንፈሳዊ ሀይል ጣልቃ ገብነት በአንድ ሰፊ ቤተሰብ አባላት መካከል በግልፅ ሊገመት በማይቻል ሁኔታ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚታላለፍ መንፈሳዊ ሥልጣን ሲሆን፣ ሥልጣኑ የተሰጠው ሰው በህይወት ዘመኑ ሁሉ ይጠቀምበታል።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የሀዲያ ህዝብ ሁለት ከፍተኛ ስልጣኖች ማለትም ገራዳ /Garaada/ እና አንጃማ /Anjaamma/ በማስመልከት ብራውከምፔር የጦር መሪ ገራዳ እና የሰላም መሪ አንጃንቾ ስዘመናት አብሮ መቀጠልና አብሮ መስራት የሀዲያን ህዝብ ለየት የሚያደርገው ገጽታው ነው በማለት ጠቅሷል (1973: 46)።

የሀዲያ ህዝብ የአስተዳደር ስርአት እንደሌሎች የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦችም በአንድ ጐሳ የበላይነት የተመሰረተ ባህርይ የለውም። ከዚህ በተጨማሪ እንደ ኦሮሞ ህዝብ የገዳ ስርአትን የመሰለ በዕድሜ እርከን የተከፋፈለ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አሰራር የሚከተል አይደለም። በሀዲያ ታሪክ አለማዊና መንፈሳዊ የመሪነት ከፍተኛ ሥልጣኖችን ሁለት የተለያዩ ግለሰቦች የሚጠቀሙ ሲሆን የስልጣኖቹም ዋነኛ ምንጮች ህዝብና መንፈሳዊ ሃይል እንደ ቅደም ተከተላቸው ናቸው።





ይህንን ስልጣን የሚጠቀሙ ሰዎች በምንም መልኩ ፈላጭ ቆራጭ እንዳይሆኑ የሚገድብ የፌደራላዊ መንግስት አወቃቀርን የሚመስል ባህላዊ የሴራ አደረጃጀት ከታች ወደ ላይ በግልጽ የተዋቀረ ሲሆን፣ በማንኛውም መዋቅር ያሉ መሪዎች ከህዝቡ በተመረጡና እያንዳንዱን ጐሳ ሲወክሉ የሚችሉ ሽማግሌዎች በንቃት በሚሳተፉበት ግልጽ የሸንጐ / Dummichcha/ ውይይት ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ።

የሀዲያ አድያም /Kingdom/ እያሉ የሚገልጹትና የሀዲያ ህዝብ ንጉሳዊ ስርአት ይከተል እንደነበረ የሚያመስክቱ በዜና መዋዕል ጸሀፊዎች የተጠቀሱት መነሻዎች እነዚህ ጸሀፊዎች በአጠገባቸው ከሚያውቁትና እጅግ ከሚያወድሱት የአስተዳደር ዓይነት ውጪ ሌላ ህዝብ ሲኖረው እንደማይችል ከመገመት የመነጨና ሌላውን በራሱነቱ ለማቅረብ ካለመፈለግ የመጣ ዘረኛ (Ethinocenteric)[41] አስተሳሰብ ውጤት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በመካከለኛው ዘመን በተለይም ከሀዲያ ህዝብ ጋር ሰፊ ግንኙነትን ሳይመሰርቱ በጥቂት ጊዜ ምልከታ ብቻ ስለ ሀዲያ ህዝብ ታሪካዊና ባህላዊ የአስተዳደር አይነት ሲጽፉ ህዝቡ ንጉሳዊ ስርአትን ይከተላል ብለው የተነተኑ ተጓዥ ጸሀፊዎችና አንዳንድ የአረብ ጸሀፊዎች መሰረታዊ መነሻቸው በምልከታቸው ወቅት የሀዲያ ህዝብ የደረሰበት የዕድገት ደረጃን ከሌሎች ተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙት ህዝቦች የአስተዳደር ዓይነት ጋር አነጻጽሮ ከመግለጽ ሲሆን እንደሚችል ይገመታል።

41 ይህ አስተሳሰብ የሌላዉን ባህል፣ ወግና እሴት በራሱነቱ የአለማክበርና አለመቀበል አካሄድን ያመለክታል።

ይህንን አመለካከት (ብረውካምፔር 1973: 47) ሲያብራራ ምንም እንኳን የሀዲያ አድያም /Kingdom/ መኖሩን የህዝብ ታሪክና ባህል ማረጋገጫ ባይሰጥም የሀዲያ ህዝብ ንጉሳዊ ስርአት ነበረው የሚል አረዳድን ሊፈጥሩ የሚችሉ ነባራዊ ጠቋሚዎች በዘመናት እንደነበሩ መግለጽ ይቻላል፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች የሀዲያ ብሄር በዘመናት የነበረውን ተጽእኖና ታሪካዊ ቦታን እጅግ የሚያጉሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በዚህ አረዳድ መሰረት የሀዲያ ህዝብ በከብት እርባታ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ብቻ የሚኖር ሳይሆን የኦሮሞ ህዝብ የመስፋፋት እንቅስቃሴ በሰሜንና በምስራቅ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አካባቢ የነበረውን ጠንካራ ሚና ከማስቀረቱ በፊት በነበሩት ዘመናት በአካባቢው ከፍተኛ የባህል እድገት ደረጃ ላይ የደረሰ ህዝብ ነበረ፡፡ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ እርሻና የዕደ ጥበብ ሙያዎች በጣም አድገዉ የነበረ ሲሆን ከአረብ አለምና ከተለያዩ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አካባቢዎች ጋር ጠንካራ የንግድ ግንኙነት እንደነበራቸው ይታወቃል፡፡ የሀዲያ ህዝብ በባሪያ ንግድ ዘመን ስልቦችን አክሞ የማዳን ወይም ጭሬሳ[42] /Cireessa/ ጥበባቸው ወደር ያልተገኘላቸው ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰውን የህዝቡን ነባራዊ የኢኮኖሚያዊና የባህል እድገት ደረጃ በመመልከት የሀዲያን ህዝብ የአስተዳደር አይነት ንጉሳዊ ነበረ ብለው የሚደመድሙ አመለካከቶች ይገኛሉ፡፡ ይህ አመለካከት ምንም እንኳን አዎንታዊ መነሻ ያለው ቢሆንም የሀዲያን ህዝብ ትክክለኛውን የአስተዳደር ስርዓት ዓይነት አይገልጽም፡፡

[42] ጭሬሳና በሀዲያ ከትንሽ ህመም ጀምሮ እስከ ቀዶ ጥገና ለሰዎችም ሆነ ለእንስሳት ህክምና የሚሰጡ ባህላዊ ሃኪሞችን ያመለክታል፡፡





በአጠቃላይ በሀዲያ ’ታሪክ ታዋቂ ከሆኑት ገራዶች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

አሸዕን ገራዳ (Asha’n Garaada)
ገደጵ ገራዳ (Gada’phph Garaada)
ወላጵ ገራዳ (Wola’phph Garaada)
ጉዶል ገራዳ (Gudoolla Garaada)
ቀቤዕን ገራዳ (Qabbee’n Garaada)
ዲደዕ ገራዳ (Diida’i Garaada)
ሰገዕ ገራዳ (Soga’i Garaada)
ጐጋል ገራዳ (Gogaal Garaada)
ዲሆዕ ገራዳ (Diiho’i Garaada)
ሀላጵ ገራዳ (Halaaphph Garaada)
ገንዝ ገራዳ (Ganz Garaada)
ሀደቦ ገራዳ (Hadaboo Garaada)
ሀዱዕም ገራድ (Hadu’m Garaada)
ሀገዕ ገራድ (Haga’i Garaada)

## 2.8. የሀዲያ ብሄር የኢኮኖሚ ሁኔታ ዳሰሳ እስከ 1974 ዓ.ም.

የሀዲያ ብሄር በረጅም ታሪኩ በኢኮኖሚ አንጻር ቅይጥ ግብርና ይጠቀም እንደነበረ የተለያዩ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ብራውከምፔር እና ጥላሁን (1999:24)` የሀዲያን ትውፊታዊ ማስረጃዎች በመጠቀም ስለ ሀዲያ ኢኮኖሚ ሲያብራሩ፣

ሲያብራሩ፣ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ሀዲያ በሁለት እንቅስቃሴዎች የተመሰረተ ኢኮኖሚ ነበረው። እነዚህም የከብት እርባታና የገብስ እርሻ ናቸው። በመሆኑም የሀዲያ ህዝብ በእርሻ ስራ ለረጅም ዘመናት ቢሳተፍም እንደ ዋነኛ ምርት ግን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራ የነበረው በገብስ እርሻ ብቻ ነበረ። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኂላ ባሉት ዘመናት ግን ከገብስ እርሻ በተጨማሪ ሌሎችንም የእርሻ ምርቶች ማምረት መልመዳቸው ይነገራል።

በተለይም ለረጅም አመታት የቀጠለው አንጻራዊ ሰላም በአንድ አካባቢ ተረጋግተው እንዲቀመጡ ማስቻሉ ተጨማሪ የእርሻ ሥራዎችን እንዲለምዱ ካስቻሉ ምክንያቶች አንዱ ሲሆን እንደሚችል ይገመታል። ከዚህ ውጪ ግን የሀዲያም ሆነ ሌሎች የአካባቢው ህዝቦች ቁጥር እየጨመረ መሄድ ሰፊ የግጦሽ መሬት እየተጣበበ እንዲመጣ ማድረጉና በእንስሳት ሀብት ላይ በተለያዩ ወቅቶች የሚከሰቱ በሽታዎች የሀብቱን ብቸኛ አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ መክተታቸው ለአዳዲስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ዕድል ፈጥረዋል።

በሀዲያ ህዝብ ረጅም ታሪክ በተለይም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በነበሩት እጠቃላይ ዘመናት የበርካታ ከብት ባለቤትነት የሀብት መገለጫ ብቻ ሳይሆን ለባለቤቱ ክብርና ማዕረግ የማስጠት ማህበራዊ ፋይዳ ነበረው። ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ከብትን የሀብትና የማህበራዊ ቦታ መገለጫ አድርጉ መጠቀም በአሁኑ ወቅት በተወሰኑ የሶሮ /sooro/ እና የባዶጐ /Baadoogo/ አካባቢዎች መቀጠል ችሏል።

ከዚህ አንጻር በሀዲያ ልጅ ሲወለድ፣ በተለይም ወንድ ልጅ ከሆነ ከብት የሀብትና የክብር ፋይዳ እንዳለው ቀስ በቀስ





ማህበረሰቡ በአጠቃላይና ወላጆች በተለይ ያስተምራሉ። በመሆኑም ለከብት ተገቢውን ዋጋ በመስጠትና ወደፊት የብዙ ከብት ባለቤት ለመሆን በመመኘት እንዲያድግ ይደረጋል። ይህ ማህበረሰቡ የሚሰጠው ተመሳሳይ ትምህርት ወንድ ልጅ ከተወሰነ እድሜ በኂላ ለሚያጋጥመው ትዳርና ራሱን ችሎ ለመኖር ከህጻንነት ጀምሮ እንዲዘጋጅ በማድረግ የነጻነት / independence/ መንፈስ እንዲያዳብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ከማስተማሪያ መንገዶች ዋነኛው በኦሽቾ (ooshshichcho) ማለትም በህጻንነት እድሜና በቤትቾ /beetichcho/ ለወንድ እና ለንድቼ /landichchee/ ለሴት ዕድሜ፣ ማለትም በልጅነት ዕድሜ መካከል ለሚገኙት ልጆች በቤተሰብ መሰረታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች አቅማቸው በፈቀደ መጠን ለሚያደርጉት ተሳትፎ በምርት ወቅት እንደማበረታቻ የሚሰጣቸው ሽልማት ወይንም ስጦታን መነሻ በማድረግ እያባዙ በወጣትነት ዕድሜ የከብት ባለቤት የሚሆኑበት እድል መፍጠር ነው። ለምሳሌ፣ እህል በሚሰበሰብበት ወቅት ለልጆች ተሳትፎ ወላጆችና ማንኛውም የመንደሩ ሰው ፎጮኦ /Foocco'o/ ወይም ትንሽ ከእህሉ በሁለት እጃቸው እየዘገኑ ልጆቹ መሸከም በሚችሉት እቃ ወይም በሰበሉት ልብስ ይሰጣቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ በአውድማ ሆን ተብሎ እንዲተርፍ የተደረገውንም እህል ልጆች አበራይተውና አዘጋጅተው እንዲከፋፍሉ ይፈቀድላቸዋል። ለዚህ ለፎጮኦ በሚያደርጉት ጥረት እግረ-መንገዳቸውን የእርሻ ስራ ይማራሉ።

የፎጮኦን ስጦታ፣ ልጆች ለቤተሰብ ፍጆታ አገልግሎት እንዲሰጡ የማይጠየቁ ሲሆን እህሉን በመሸጥ አብዛኛውን

ጊዜ ሴት ዶሮ ገዝተው እንዲያረቡ ወላጆች ይመክሯቸዋል። ዶሮዎችን እቤት ውስጥ ከሚጣል እህልና እንክርዳድ በመቀለብና በማስፈልፈል በርከት ያሉ ዶሮዎች ባለቤት ይሆናሉ። እነዚህ ዶሮዎች ለገበያ ቀርበው ጥሩ ገቢ ማስገኘት የሚችሉበት ዕድሜ ሲደርሱ በመሸጥ በጐችን ወይንም ፍየሎችን እንዲገዙ ይደረጋሉ። የተገዙትን በጐች ወይም ፍየሎች ልጆች ከራሳቸው እኩል ስለሚንከባከቧቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተባዝተው ይሸጡና ጥጃ /Wee'ichcho/ እንዲገዙ ይደረጋል። በዚህ ሂደት ልጆች የንብረት ባለቤት በመሆን ለወደፊት ህይወታቸውና ለሃላፊነት እራሳቸውን እንዲያዘጋጁም ይበረታታሉ።

በሀዲያ የአንድ ግለሰብ የከብት ብዛት እያንዳንዱን ከብት በመቁጠር በተደረሰ ሙሉ ቁጥር አይነገርም። ይልቁንም የተለያየ ብዛት ያላቸውን የከብት ስብስቦች ታሳቢ በማድረግ የከብት ብዛትን የሚወክል አራት የተለያዩ መጠሪያዎችን ይጠቀማሉ። እስከ 20 ከብት አንድ ግለሰብ ሲኖረው ይህ በጥቅሉ *ፎርገሳ* /Foorgassa/ ተብሎ ይጠራል። እስከ 80 ከብት አንድ ግለሰብ ሲያረባ የግለሰቡ የከብቶች ብዛት በጥቅሉ *ጉበንታ* /Gubanatta/ ተብሎ ይጠራል። የአንድ ግለሰብ እስከ 100 የማይደርሱ ከብቶች በጥቅሉ *ጥቤ* /Xibbe/ የሚል መጠሪያ ይሰጣቸዋል። እስከ 1000 ለሚደርሱ ከብቶች አንድ ግለሰብ ባለቤት ከሆነ፣ ከብቶቹ በጥቅሉ *ኩማ* /Kuma/ ተብሎ ይጠራል።

የአንድ ግለሰብ የከብቶች ብዛት ሁለቱን ከፍተኛ ቁጥሮች/ ጥቤና ኩማ/ ሲደርሱ በሀዲያ ህዝብ ባህል የግለሰቡን ደረጃ ለማክበርና የክብር ማዕረግ ለመስጠት የሚያስችል ባህላዊ ስነ ስርአት ይደረጋል። ይህ ባህላዊ ስነ ስርአት *ወገና* /Wogana/





ተብሎ ይጠራል። *ወገና* የሚለዉ *ቃል* በጥሬ ትርጉሙ[43] በከብቶች ላይ በስነ-ስረአቱ ወቅት የሚረጨዉን በማርና በወተት የተበጠበጠ ዉሃን የመርጨትን ስነ-ስርአት ያመለክታል።

የወገና /Wogana/ *ሥነ ሥርዓት* የሚካሄድበትን *መሠረታዊ* ምክንያት የሀዲያ ሽማግሌዎች ሲያስረዱ፤ አንድ ግለሰብ መቶና ከዚያም በላይ የሆኑ ከብቶች አርብቶ ለማስቆጠር በርካታ የሆነ ፈተናዎችን ማለፍ የሚያስችል ልበሙሉነት፣ ቁርጠኝነትና ጽናት እንዲኖረው ይጠበቃል። ከዚህም በተጨማሪ ለከብቶች ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ወቅትን ጠብቆ ወደተለያዩ ቦታዎች መዘዋወር ይጠበቅበታል።

የቤት እንስሳትን በተለይም ከብቶችን ይዞ ቋሚ የመኖሪያ አካባቢን በጊዜያዊነት በመልቀቅ ግጦሽና ውሃ ወደሚኙበት ሩቅ አካባቢ የሚደረገው ጊዜያዊ ስደት /ጉዞ/ ደርበኣ /Darba'a/ ተብሎ ይጠራል። ከዚህ አስተሳሰብ የተነሳ መቶና ከዚያም በላይ ከብቶች በገንዘብ ከገበያ በመግዛት ወይም በሌሎች ከልፋት ነጻ በሆኑ መንገዶች ባለቤት በመሆን የወገና *ሥነ ሥርዓት* እንዲደረግና ተገቢውን ማዕረግ እንዲሰጥ መጠየቅ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ እንደ ነውር ይቆጠራል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የሶሮ ባለባቶች የሆኑት ግራዝማች ሃይሌና ቀኛዝማች ቅንጣሞ[44] ምንም እንኳን ከመቶ በላይ ከብቶች ባለቤት መሆን ቢችሉም ባለቤትነቱ ከከብቶች ጋር ተንከራተው፣ አርብተውና የተለያዩ ፈተናዎችን አልፈው ያገኙ ስላልነበረ ባለመቶ ከብት ወይም ጥባሞ /Xibbaamo/ መባል ቢፈልጉም፣ የሀዲያ ሴራ /Seera/ ነፍጓቸዋል።

[43] ይህን ትርጉም የነገረን ዘነበ ዮሃንስ ካንዲዶ ነዉ።

[44] ይህንን አስተያየት የሰጡት የግራዝማች ሃይሌ ልጅ የሆኑት የተከበሩ አቶ ጌታቸዉ ሃይሌ ናቸዉ።

ለወገና /Wogana/ ሥነ ሥርዓት ወይንም ከመቶ /Xibba/ ጀምሮ የከብት ሀብትን ለማስቀጠር አቅም የፈጠረ የሀዲያ ከብት አርቢ ለሥነ ሥርዓቱ ከሁለት ዓመታት በፊት ጀምሮ አቅዶ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል:: በዚህ ከሁለት ዓመታት በላይ የሚፈጀው የዝግጅት ጊዜ ለወገና ሥነ ሥርዓት የሚያስፈልጉ ነገሮች ለምሳሌ፤ ቅቤ፣ማር፣ ለእርድ የሚሆኑ በሬዎች፣ ለሥነ ሥርዓቱ የሚሆኑ አዳዲስ ቤቶችና ድንኳኖች ይዘጋጃሉ::

ዝግጅቱ በብቃት ተዘጋጅቶ የሚያበቃበት ጊዜም ተሰልቶ ለወዳጅ ዘመድ የሥነ ሥርዓቱ ማስፈጸሚያ ቀናት ተወስኖ ጥሪ ይተላለፋል:: ጥሪ ሲተላለፍ በሥነ ሥርዓቱ ወቅት ወዳጅ ዘመድ ይዞ የሚመጣውን ስጦታ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ በመስጠት ይሆናል:: የመቶና ከዚያም በላይ ከብት አስቀጣሪው /Woganaancho/ ዘመዶች በምኔ / Mine/ ወይም በሞሎ /Moollo/ ተደራጅተው የተለያየ መጠንና ዓይነት ያለውን የከብት ስጦታና ወጭታ /Wocitaa/ ያዘጋጃሉ::

*በወገና* እለት *የወገናንቾ* ከብቶች በአጠቃላይ በአንድ *ጋድራ* / Gaadira/ ወይም በረት ውስጥ እንዲሰበሰብ ይደረጋል:: የከብቶች ቆጠራ ሥነ ሥርዓት የሚካሄደው ቀድመው የወገናና ሥነ ሥርዓት በመፈጸም የከብት ባለሃብትነትን ክብር ባገኙ የሀዲያ የተከበሩ ሰዎች (*መሃራኖ* /Mahaaraano/) ይሆናል::

ቆጠራው የሚካሄደው በአካባቢው በሚገኘው ትልቅ ወንዝ አጠገብ ሲሆን፣ ለዕለቱ ቆጠራ የሚሆኑ ጤነኛ የሆኑትና ከጥጃ ውጪ የሆኑ በጥሩ አቋም ላይ የሚገኙ አጠቃላይ





ከብቶች በጧቱ ወደ ወንዙ መነዳት ይጀምራሉ:: ወደመቁጠሪያ ቦታ ለመሄድ ከብቶቹ እንዲንቀሳቀሱ የባለሀብቱ ከብት የተሰበሰቡበትን *ጋድራ* /Gaadira/ የሚከፍተው *የወገንቾ* ወይም የአስቀጣሪው የመጀመሪያ ልጅ ወይም ዎና /Wona/ ሲሆን፣ ቀድሞ ከጋድራ የወጣውን ከብት ይሸለማል:: ከሁሉም ከብቶች በመጨረሻ ከጋድራ የወጣው ከብት ደግሞ የወገናንቾ የመጨረሻው ልጅ ወይም *እልሙቾ* /Ilmuchcho/ እንዲወስደው ይደረጋል::

ከብቶቹ ወደሚቆጠሩበት ወንዝ ሲጓዙ ከከብቶቹ ባለቤቶች መካከል ባል /Aro'o/ በበቅሎ ተቀምጦ ሚስት /Mi'nama/ በፈረስ ተቀምጣ ይንቀሳቀሳሉ:: የዕለቱ ሥነ ሥርዓት ታዳሚዎች በጉዞ ወቅት የሚከተለውን ዘፈን እየዘፈኑ ይጓዛሉ::

*መሴሄ አወንሴሄ*

*Massehee Awansehee*

*እየሄድን እየመራችሁን*

በዚህም ለሥነ ሥርዓቱ ያላቸውን ጉጉትና ክብር ይገልጻሉ:: ከብቶች ተጉዘው ቆጠራው ወደምካሄድበት ወንዝ ሲደርሱ ወደ ወንዙ እንዲገቡና እንዲሻገሩ በማድረግ ለቆጠራው ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ::

ተቆጥረው መቶና ከዚያ በላይ ወይም ሺህና ከዚያም በላይ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ከብቶቹ ላይ ወተት፣ ማርና ቅቤ ተበጥብጦ ይርከፈከፋል ወይም ይረጫል:: እዚያው በከብቶቹ ባለቤት ቁመት ልክ ጉድጓድ ተቆፍሮ ወተት እንዲሞላበት

በማድረግ ግለሰቡ ወተት በተሞላበት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ እንዲሰምጥ ይደረጋል፡፡ በዚህም ወቅት የሀዲያ ህዝብ ምን ያክል የተትረፈረፈ የእንስሳት ሀብት እንዳለው ለማመልከት የሚከተለው ዘፈን ይዘፈናል፡፡ በዘፈኑ ወቅት የግለሰቡ ዘርና ዝና ይሞገሳል፡፡

*ሸንበለለዮኔ*

*Shambalalayyonne*

*የተትረፈረፈ ሀብት ነው!*

በˆለቱም ለተገኙ *ታዳሚዎች* *የጨለለቃ* /Calalaqaa/ ደረጃ ወይም በሀዲያ ባህል ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ *ሉባ* /Luba/ ወይም ግብዣ ይቀርባል፡፡ ግብዣው በተመሳሳይ ደረጃ ለተከታታይ በርካታ ቀናት ይቀጥላል፡፡ የሀዲያ ተዋቂ ባለማዕረጐች ፣ የቀደሙና በከብት ሀብት የክብር ማዕረግ ያገኙ ግለሰቦች፣ የየጉሳው ተጠሪ ሽማግሌዎች አዲሱን የከብት ባለሀብት መርቀው አዲሱን ማዕረግና ማህበራዊ ቦታውን ያጸድቃሉ፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግለሰቡ በከብት ብዛት የደረሰበት ደረጃ የሚያመለክት ተቀጥላ ማዕረግ ከስሙ ጋር አብሮ እንዲጠቀም ይፈቀድለታል፡፡ በመሆኑም ባለመቶ ከብት ወይም ባለሽህ ከብት (*ጥባሞ* /Xibbaamoo/ ወይም *ኩማሞ* /Kumaamo/) እንደቅደም ተከተለቸው መለያው እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ግለሰቡ በህዝቡ ውስጥ በሀብቱ ምክንያት ሊሰጠው የሚገባውን ማህበራዊ ደረጃ ለማመልከት ባለብዙ ክብር (*መሃራንቾ* /Mahaaraancho/) የሚል ማዕረግ ይሰጠዋል፡፡ የማዕረጉን አሰጣጥ አስመልክቶም *ሄቦቶ* /Hebbootto/ የሚል ባህላዊ ጭፈራ ይጨፈራል፡፡ *የመሃላኖ* /Mahaallano/ ማዕረግ አሰጣጥን አስመልክቶ ብራውካምፔሪና ጥላሁን (1999፡ 56) ሲያብራሩ የሚከተለውን ብለዋል፡፡





*በሀዲያ አንድ ሰው ሀብቱ ሲበዛ በተለይ የከብቶቹ ብዛት ከመቶ በላይ ወይም ከአንድ ሺህ በላይ ሲደርስ ግለሰቡ የመሃርማ* /Maharimma/ *ሥነ ሥርዓት ያዘጋጃል፡፡ ለዚህም ሥነ ሥርዓት እጅግ በጣም ብዙ መጠንና ጥራት ያለው ድግስ ይደገሳል፡፡ ከዚያም አጠቃላይ ዘመዶቹን፣ የአካባቢውን ሽማግሌዎችና ከአጠቃላይ ሀዲያ ተዋቂ ግለሰቦችን ይጋብዛል፡፡ ግብዣቸውን ከበሉና ከጠጡ በኋላ ሄቦቶ* / Hebbootto/ *የሚባለውን የሀዲያ ባህላዊ ጭፈራ ለየጨፈሩ ባለሀብቱን በላዩ ላይ ወተት እና ማር የተጨመረበት ውሃ እያፈሰሱ ይመርቁታል፡፡ በዚህ የምርቃት ወቅት ለባለሀብቱ የመሃራንቾ* / Mahaaraancho/ *ማዕረግ ይሰጡታል፡፡ በሀዲያ ህዝብ ትውፊታዊ መረጃ መሠረት ከአንድ ሺህ በላይ ከብቶችን በማስቆጠር የመሃራንቾ* /Mahaaraancho/ *ማዕረግ የተሰጣቸው ግለሰቦች*[45] *ጥቂት ናቸው፡፡*

በሀዲያ ባህል መሠረት አንድ ግለሰብ በበሽታ ምክንያት ያፈራውን አጠቃላይ የከብት ሀብቱን ካጣ ይህ አሳቃቂ ሁኔታ *ብጭኡንጃ*[46] /Bicc'uunja/ ተብሎ ይጠራል፡፡

ከከብት እርባታ ቡተጨማሪ የሀዲያ ህዝብ በእርሻ ሥራ የተመሠረተ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ያደርጋል፡፡ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ የእርሻ ሥራ ዓይነቶችና ለእርሻ ሥራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ባሉት ዘመናት እየበዙና እየተሻሻሉ መምጣታቸው ይነገራል፡፡ በተለይም በ19ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻው አሥር አመታት አካባቢ ማለትም ከ 1889 እስከ 1891 ዓ.ም. ድረስ የተከሰተው እጅግ አደገኛ የከብት በሽታ የሀዲያን ህዝብ ለሸዋው ወራሪ ሀይል እንዲንበረከክ

[45] ገደጽ ገራድ ሶቦቆ ጉሎ፣ ቦንኬሌ፣ ደሪሎ እና ሌሎችም፡፡

[46] ምንአልባትም ይህ ቃል ለከብት ማገጃ የሚዉለዉን በትር መጠቀም አለመቻልን የሚያመለክት ይመስላል፡፡

ከማድረጉም በተጨማሪ ከእንስሳት እርባታ ውጭ ለእርሻ የተሻለ ትኩረት እንዲሰጥ አስገድዶታል፡፡ የሸዋው ወራሪ ሃይል የሀዲያን አካባቢ ከመቆጣጠር ጋር ተያይዞ በበሬ የማረስ ዘዴ ሊተዋወቅ ችሏል፡፡ ከሀዲያ ህዝብ ውስጥ በበሬ የማረስን ዘዴ ቀድመው የሰመዱት የሌሞ /Leemo/ ሀዲያዎች መሆናቸውን የሀዲያ ሽማግሌዎች ያወሳሉ፡፡

የእርሻ ሥራ በዓይነትም ሆነ በአስተራረስ ዘዴ እየበዛና እየተሻሻለ ሲመጣ በተለይም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ተዋቂ ከሆኑት የምርት ዓይነቶች ውስጥ እንሰት፣ ጤፍ ፣ ስንዴና ሌሎችም የጓሮ አትክልት ይጠቀሳሉ፡፡ የጤፍ እርሻ ወደአካባቢው የመጣው አዲስ ሰመጡ ገዥዎች ከባህላቸው ጋር አብሮ የሚሄድ የምግብ /እንጀራ/ ፍላጐት ለማሟላት በግብር መልክ የሀዲያ ገባሮች ጤፍ እንዲያቀርቡ ስለሚጠበቅባቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡

እንሰት በሀዲያ ህዝብ ዘንድ ለምግብነት መዋል የጀመረው ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ሲሆን የእንሰት የሥነ ምግብ ጠቀሜታ አስተሳሰብና የአዘገጃጀት ዘዴዎቹ ለሀዲያ ህዝብ የተዋወቀው የአካባቢው ማህበረሰብ ከሆኑት ከጉራጌ፣ ከከንባታና ከወላይታ ነበረ፡፡

ህዝቡ እንሰትን ለምግብነት መጠቀም ከጀመረበት ዘመን አንስቶ የእንሰት ዘርፍ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን መገንዘብ ጀምሯል፡፡ ከዚህም የተነሳ በደርግ ሥርዓት በሠፈራና በመንደር ምሥረታ ኘሮግራሞች ምክንያት ህዝቡ ወደ ስንዴ እና ሌሎችም በዘመኑ መንግሥት ወደሚፈልጋቸው ምርቶች ከማዘንበሉ በፊት ክፍተኛ ትኩረት በመስጠት በጓሮው እንሰትን በሥፋት ይተክል እንደነበረ ይታወቃል፡፡





እንሰት፣ ለቤት እንስሳት በተለይም ለከብቶች፣ በጐችና፣ ፍየሎች፣ ለጋማ ከብቶች ዋነኛ የምግብ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዱር እንስሳትም እንደ ጃርት ያሉት እንሰትን በስፋት ለምግብነት ይገለገላሉ፡፡ ለሰዎች የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ከእንሰት ውጤቶች የሚሰሩ ሲሆን ከእንሰት ተረፈ ምርቶች የተለያዩ አይነት የመገልገያ ዕቃዎችም ይሰራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የእንሰት ውጤቶች ለሰውና እንስሳት የተለያዩ በሽታዎችንና ጉዳቶችን ለመፈወስ በሰፊው አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡

አበበች (2009፡ 101-103 ) እንዳመለከተችው በሀዲያ ወደ 60 የሚጠጉ የእንሰት ዝርያዎች ሲኖሩ እነዚህም ወንዴና ሴቴ ተብለው ይከፋፈላሉ፡፡ አበበች ኤርጐጐ (2009) ከዘረዘረቻቸው የእ'ንሰት ዓይነቶች መካከል፡-

*ድርቦእ፣ ለስቁላ፣ ግሸራ፣ ማርቤ፣ ቁእና፣ ጦሮራ፣ ጊሞቦእ፣ ድሸእ፣ ዞቢራ፣ ኦይና፣ መርዛ፣ ኡንጃማ፣ ከርቃሬ፣ ቀዳል ኦኒያ፣ ሔመች ኦኒያ፣ ሰቁኤ፣ ኦገዴ፣ ሰፐራ፣ ቀሸቀሺያ፣ አስታራ፣ ለንድዌሳ፣ ማንዱሉቃ፣ አንኮገና፣ ለዕሜሳ፣ ቦዕሌ፣ ቆምቦቲራ፣ ሽቴ ፣ ሀይዎና፣ ወሽመዳ፣ ጎዞዳ፣ ገሪያ፣ ቁኒዋራ፣ በዳዴኤ እና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡*

የእ'ንሰት ተክል ለሰው ልጆች ምግብነት ሲውል በጥቅል ስሙ ዋሳ /Waasa/ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ተክል ዋሳ ወይም ቆጮ ሆኖ ለሰው ልጅ ምግብነት ለመዋል የተለያየ ደረጃ ያለውን የዕድገት ሂደት ለማለፍ በአማካይ ከ7-8 ዓመታት ጊዜን ይፈጃል፡፡ የእንሰት ተክል የሚባዛው በስሩ ሲሆን የማባዛት ስራ የሚጀመረው ስሩን በባህላዊ መንገድ ለብዜት በማዘጋጀት

ሰመኖሪያ ቤት ቅርብ በሆነው የጓሮ መሬት ወይንም ሀረፎኦ[47] /Harafo'o/ ውስጥ በመቅበር ነው።

ይህ መሬት ውስጥ ሰብሴት የሚቀበር የእንሰት ሥር ዱቦኦ / Dubbo'o/ ተብሎ ይጠራል። ሰመኖሪያ ቤት በጣም ቅርብ በሆነ አካባቢ /ጓሮ/ በመቀበሩ ምክንያት ዱቦኦ /Dubbo'o/ የተሰየዩ ባህላዊ ማዳበሪያዎችን ሰምሳሌ፤ አመድ፣ እበትና የቤት ጥራጊን በቀላሉና በቅድሚያ የማግኘት ዕድል ይኖረዋል። በመሆኑም ቤተሰብ ለዱቦኦ ሁሰንተናዊ እንክብካቤ በማድረግ ያሳድጋል። አንድ ዱቦኦ በርካታ የእንሰት ተክሎችን ማፍራት ይችላል። እነዚህ ከአንድ ዱቦኦ የሚበቅሉ በርካታ የእንሰት ተክሎች በጋራ ፊሾኦ /Füshsho'o/ ተብለው ይጠራሉ። ፊሾኦን /Füshsho'oo/ ከዱቦኦ በማላቀቅ ሰፋ ባሰ መሬት ላይ ሰተጨማሪ ዕድገታቸው በሚያመች ሁኔታ በአንድ ጉዳጓድ ውስጥ አራት በአንድ ላይ ይተከላሉ።

እነዚህ አራት በአንድ ሆነዉ የሚተከሉት በእንሰት የሁሰተኛውን የዕድገት ደረጃ የደረሱት ሰማ /Sima/ ተብለው ይጠራሉ። ከአንደ ዓመት ቆይታ በኋላ አራት በአንድ ያደጉት ሰማዎች/Sima/ ወደ ሌላ ሰፊ ቦታ ተዛውረው እያንዳንዳቸው እራሳቸውን ችሰው እንዲተከሉ ይደረጋል። በዚህ ደረጃ የሚገኝ እንሰት ኤሮኦ /Eero'o/ ተብሎ ይጠራል። ኤሮኦ / Eero'o/ ሰአንድ ዓመት በከፍተኛ እንክብካቤ በተተከለበት ሰፊ ቦታ ካደገ በኋላ ከዋናው የእንሰት እርሻ ሰሰዎችና ሰእንስሳት ምግብነት የተቀነሱት እንሰቶችን ሰመተካት በተነሱት ቦታ ከሌሎች ትላልቅና ሰምግብነት እየተዘጋጁ ካሉት የእንሰት

[47] ይህ ፈሳሽ የሆነዉ የቤት እንስሳት ሽንት ከበረት (ጋድራ) በቀጥታ ወደ ጓሮ የሚወጣበት መንገድ ነዉ።



የሀዲያ ህዝብ ታሪክና ባህል

ተክሎች ጋር ተቀላቅሎ ይተከላል። ይህ አንድ የእንሰት ተክል ሰምግብነት የሚዘጋጅበትና ከዕድሜውም በአንድ ቦታ ራጅሙን ጊዜ የሚያሳልፍበት ነው። ከላይ የተመሰከተው የእንሰት ተክል የዕድገት ሂደትን እንያንዳንዱ ደረጃ ከሚፈጀው ዕድሜ ጋር ሲቀመጥ እንደሚከተሰው ይሆናል።

| የዕድገት ደረጃዎች | የሚፈጀው ጊዜ |
| --- | --- |
| ዱቦኦ /Dubbo'o/ | አንድ ዓመት |
| ሰማ /Sima/ | አንድ ዓመት |
| ኤሮኦ /Eero'o/ | አንድ ዓመት |
| ዌሳ /Weesa/ | ከሶስት እስከ አራት |

እንሰት ሰምግብነት ከደረሰ በኋላ ተዘጋጅቶ /ተፍቆ/ ሰማዕድ እስከሚቀርብ ድረስ የተሰያዩ መሳሪያዎች በተሰያዩ ደረጃዎች ያስፈልጋሉ። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

| | |
| --- | --- |
| ቀንጩሌኤ /Qunculle'e/ | የእንሰትን ከባ ሰመፋቅ ሰማዘጋጀትና ዝግዛግ/አግድም/ ሰመቁረጥ የሚጠቅም መሣሪያ |
| ሜታ /Meeta/ | ከሰፊ የእንጨት ጠውላ የሚሰራና የሚፋቅ ከባ ማስደጋፊያ መሣሪያ |
| ሰሳ/Sissa/ | ከቀርከሃ የሚዘጋጅ የከባ መፋቂያ መሣሪያ |

| | |
|---|---|
| ቁዎኦ /Qewwo'o/ | ከእንጨት የሚሰራና ከጫፉ ወፈር ያለ ጥርስ ያለው የእንሰት ሥር ወይም ሀዕምቾ /Ha'mmichcho/ የውስጠኛው ክፍል ብቻ ለመቆፈር ወይም ለመጨፍጨፍ የሚያገለግል መሣሪያ |
| አንጫ /Aanca/ | የእንሰት ተረፈ ምርት ወይም ቃንጫ ሲሆን ቆሙን ከውሃ /Gaana/ ለመለየትና ለማድረቅ ያገለግላል |
| ሞጭናንቾ /Moocinaancho/ | ከቆሙ ተጨምቆ የሚወጣውን ውሃ ወይም ጋና /Gaana/ ማጠራቀሚያ ዕቃ |
| ጐንጋ /Gonga/ | የደረቀ ቆሙ መቁረጫ ሰፊና ትልቅ የኮርች እንጨት ጉማጅ፤ ብዙውን ጊዜ ርዝመቱ ከአንድ ሜትር አይበልጥም። |
| መሽአ /Mashsha'a/ | የቆሙ መቁረጫ ሰፊና ትልቅ ቢላዋ። |

ከከብት እርባታና ከእርሻ ስራ በተጨማሪ የሀዲያ ህዝብ በንግድ እንቅስቃሴም የራሱ የሆነ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ተሣትፎ አለው። በሀዲያ የንግድ እንቅስቃሴ ሁለት መሠረታዊ መልኮችን የያዘ ሲሆን እነዚህም በሀዲያ መካከል የሚደረግ የእርስ በርስ የንግድ ልውውጥና የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦችና ከኢትዮጵያም ውጪ ካሉት የንግድ አጋሮች ጋር ያደርግ የነበረውን የንግድ ልውውጥን ያጠቃልላል።

በሀዲያ ህዝብ ጥንታዊ የረጅም ርቀት የንግድ እንቅስቃሴ በባሪያ ንግድ ላይ የነበረው የተለየ ተሳትፎ ተጠቃሽ ነው። የአረብ ጸሀፊዎች የሀዲያን አካባቢ በዛሬው ኢትዮጵያ ደቡባዊ አካባቢ ወሳኝ ሚና የነበረው የንግድ ማዕከል እንደነበረ ገልጸዋል። በተለይም እብን ሳይድ የተባለ የአረብ ጸሀፊ





የሀዲያን በባሪያ ንግድ ላይ የነበረውን የተለየ ተሣትፎና በረጅም ርቀት ንግድ ላይ የነበረውን ወሳኝ ሚና ሲገልፅ ሀዲያ ስልብ /ብልቶቻቸው የተቆረጡባቸው/ ተደርገው ለሽያጭ የሚዘጋጁ ሰዎች ቁስላቸው እንዲድን የህክምና እርዳታ የሚደረግላቸው ዋነኛ ቦታ እንደነበረ ገልጿል (ታደሰ፣ 1972: 86)።

በሀዲያ ባህላዊ ሀኪሞች (ጭሬሳ /Cireessa/) ታክመው የዳኑ ሰዎች ለውጭ ንግድ የሚሸጡበት ዋነኛ ማዕከልም ሀዲያ መሆኑን የአረብ ጸሀፊዎች ገልጸዋል። ከተለያዩ የደቡብ አካባቢዎች ተገዝተው በሀዲያ አገር ህክምና ተደርጐላቸው ለውጪ ነጋዴዎች የተሸጡ ባሮች በዋናነት በዘይላ የባህር በር በኩል ወደ አረብ አገሮችና የሰሜን ምሥራቅ የአፍሪካ አገሮች ይጋዙ እንደነበረ ተመሳሳይ የአረብ ጸሀፊዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

እንደማገኘውም የኢትዮጵያ ህዝብ በሀዲያ የንግድ እንቅስቃሴ ዋነኞቹ የመገበያያ መሣሪያዎችና ዘዴዎች በየዘመኑ ይለዋወጡ ነበር። በዚህ አንፃር ረጅም ዘመናት ታዋቂ የነበረው የመገበያያ ዘዴ ዕቃን በዕቃ የመለዋወጥ /barter/ ዘዴ ነበረ። ከምኒልክ ወራሪ በፊት በነበሩት ዘመናት አሞሌ ጨው ወይም ሜርሙአ /Merco'o/ እና የማሪያ ቴሬሳ ታለር (በውስን ደረጃ) የመገበያያ መሣሪያዎች ሆነው አገልግለዋል። ከንጉሥ ምንልክ ወረራ በኋላ በነበሩት ዘመናት በሀዲያ አካባቢ ከብረት የተሠሩ ሳንቲሞች ወይም ተሙና /Tamuna/ የሚባሉት የመገበያያ መሣሪያዎች ሆነው ማገልገላቸው ይነገራል።

የሀዲያን ህዝብ ከሌሎች የአካባቢ ህዝቦች ጋር የሚያደርጋቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች በቅርበትና በፍላጐት መመሳሰል ላይ የተመሠረተ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ፣ የቀቤና ሀዲያዎች ከጂማና፣ ሊሙ አናሪያና ከሌሎች የአካባቢው የጉራጌና የኦሮሞ ህዝቦች ጋር ጠንካራ የሆነ የንግድ ትስስር መሥርተው ኖረዋል፡፡ የባደዋቾ ሀዲያዎች ከወላይታ እና ከከምባታ ህዝብ ጋር የንግድ ትስስራቸው ጠንካራ ነው፡፡ የሶሮ ሀዲያዎች ከከምባታና ከወላይታ ህዝብ ጋር ጠንካራ የንግድ ግንኙነትን መሥርተው ይኖራሉ፡፡ የስልጤ፣ የጉራጌና የከምባታ ህዝብም ከሌሞ ሀዲያዎች ጋር ያላቸው ጠንካራና ብዙ ዘመናትን ያስቆጠረ የንግድ ትስስር በሀዲያ ታሪክ ተጠቃሽ ነው፡፡

ከጣሊያን ወረራ ጀምሮ የሀዲያን ህዝብ ከሌሎች የሩቅ አካባቢ ህዝቦች ጋር ሊያገናኙ የሚችሉ መንገዶች መሠራት መጀመራቸውና የዘመናዊ ትራንስፖርት ተጠቃሚነት ደረጃ በደረጃ እየተሻሻለ መምጣት ለንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋትና መጠናከር ያበረከተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ ከአለምገና በሆሳዕና አቋርጦ እስከ ወላይታ ሶዶ ድረስ የሚዘልቀው መንገድ መሠራቱ ከላይ ለተጠቀሰው ሁኔታ ጥሩ ምሳሌ መሆን የቻለ ክስተት ነው፡፡ የዚህ መንገድ ግንባታ እውን እንዲሆን የሀዲያ ህዝብ ከፍተኛ የገንዘብና የጉልበት አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡

በአጠቃላይ የሀዲያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተለያዩ ነገሮች የተመሠረተ ቢሆንም የከብት እርባታና ሌሎችም የእርሻ ሥራዎች የኢኮኖሚው መሠረቶች ሆነው ቆይተዋል፡፡





# ክፍል 3፤ የሀዲያ ሴራ [48]

## 3.1. የሀዲያ ሴራ ምንነት

ሴራ /Seera/፣ በሀዲያ ማህበረሰብ ውስጥ የህዝቡን ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የግንኙነት ሂደትና ሁኔታ እንዲሁም መዋቅርና ስርአት የሚወስን ማህበራዊ ህግ ወይንም ደንብ ነው፡፡ የሀዲያ ሴራ በአባላቱ ላይ ማህበራዊ አስገዳጅነት ያለው ሆኖ ተፈጻሚነቱን የሚከታተሉና የሚቆጣጠሩ ተቋማት በየደረጃው ያሉት ስርአት ነው፡፡ በሀዲያ ማህበረሰብ ውስጥ ማንኛውም የህይወት መስክ ከሴራ ስርአት ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡

ፍቅርና ጋብቻ፣ ግጭትና እርቅ፣ ዝምድናና የቤተሰብ ግንኙነት፣ የሀብት ውርስና የንብረት ክፍፍል፣ ጓደኝነትና የእኩያሞች ቀልድ፣ ስራና የስራ ማህበራት፣ የመዝናኛ ድግሥ፣ ጨዋታዎችና ስፖርት፣ አደንና የአካባቢ እንክብካቤ፣ ትምህርትና ሃይማኖት የመሳሰሉት በአጠቃላይ የሴራው አካላት ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የህይወት መስክ፣ እያንዳንዱ ክስተትና ሁኔታ በሴራ ስርአት የሚታይበት ደንብ፣ መዋቅርና ባለስልጣን ያለው ነዉ፡፡ የሴራ ስርዓት መሰረታዊ መርህ እያንዳንዱ ሀዲያ /Hadiyyichcho/ የማህበረሰቡን የሞራል ደረጃዎች ታሳቢ አድርጐ እንዲኖር የሚጠበቅ ሲሆን ሃላፊነት ከግለሰብ ይልቅ ለአጠቃላይ ማህበረሰብ የሚሰጥ ስርዓት ነው፡፡

በዚህ መሰረት ልማትንም ሆነ ጥፋትን የሀዲያ ህዝብ በየደረጃው እንዲጋራ ስለሚጠበቅ ማህበረሰቡ በበኩሉ ደግሞ

[48] ሴራ የሚለዉ ቃል በደቡብ የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህላዊ የአስተዳደር ስርአታቸዉን የሚገልጹበት ጽንሰ-ሀሳብ ነዉ (ባህሩ እና ፓዉሰዋንግ 2006)

እያንዳንዱን ሀዲያ የሀዲያን ሴራ የማስተማር ግዴታ አለበት፡፡ በሀዲያ ሴራ እያንዳንዱ ሀዲያ ለእውነት የቆመና ሀቀኛ እንዲሆን የሚጠበቅ ከመሆኑም በላይ ለሌሎች ተገቢውን ክብር መስጠትን ለወጣቱ ትውልድ ያስተምራል፡፡ ከምንም በላይ የሀዲያ ሴራ እውነት ቦታውን እንዳይስትና እንዳይጠፋ ማንኛውንም ዋጋ መክፈልን ያስተምራል፡፡ የሀዲያ ሴራ ለእኩልነትና ለሴራው ደንቦች የበላይነትን ቅድሚያንና ትልቅ ቦታን የሚሰጥ ስርአት ነው፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ሀዲያ በሴራ እኩል ይዳኛል፡፡ ምንም እንኳን ሴራ ከእያንዳንዱ ጉዳይ ጋር የሚያያይዛቸው ውሳኔዎች፣ ደንቦችና ቅጣቶች የዘመናትን ለውጥና አዲስ እድገትን መሰረት በማድረግ ማስተካከያዎች እየተደረጉባቸው ቢኖሩም የሴራ መገለጫ የሆኑት መሰረታዊ መርሆዎች ለምሳሌ፤ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮቹ፣ የሴራ የበላይነትና በሁሉም ሀዲያ ላይ ተፈጻሚነቱ፣ ማህበራዊ ሃላፊነትን ማስቀደሙና የመሳሰሉት ግን እራሳቸውን አስጠብቀው እስከአሁን ዘመን ድረስ ዘልቀዋል፡፡

በሀዲያ ሴራ፣ ማንኛውም ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ወይም በተለያዩ መዋቅር መሪዎች ብቸኛ ፍላጐት የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲያገኙ አይደረግም፡፡ ምንም ከባድና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ እንኳን ቢሆን በሀዲያ ሴራ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስምምነትና በመተማመን ነው፡፡ ይህ የሴራ አሰራር፣ እውነት እንዲከበርና ዘላቂ ሰላም በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሰፍን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

እላይ የተጠቀሱት የሀዲያ ሴራ ባህሪያት ስርአቱ ለለውጥ ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ብቃት ያለው መሆኑን





ያመለክታሉ፡፡ ምንም እንኳን መጠነኛ ልዩነቶችን ቢያንጸባርቅም የሀዲያ ሴራ በተመሳሳይ ዘመን ለሚከሰት ተመሳሳይ ጉዳይ፣ ተመሳሳይ የሆነ ውሳኔና ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በቦታና በግለሰቦች ፍላጐት የተመሰረተ ለፊ የአሰራር ልዩነቶችና ዝብርቅርቆች እንዳይከሰቱ ዋነኛ መሳሪያ ተደርጐ የቀጠለው የሀዲያ ሴራ የውሳኔና የምላሽ አሰጣጥ ስርአት ራሱ ነው፡፡

የሀዲያ ሴራ ሁሉንም ሀዲዮች እኩል አድርጐ የሚወስድ ሲሆን ሰዎችን /ሀዲያዎችን/ በተሰማሩበት የስራ መስክ፣ ከሀዲያ ጎሾዎች ውስጥ አባል የሆኑበትን ቤተሰብ ወይም የሚኖሩበትን አካባቢ መሰረት ያደረገ ማንኛውንም ልዩነት አያስተናግድም፡፡ ነገር ግን እንደብዙዎቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በሀዲያ ውስጥም ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ፤ ከእነዚህም መካከል ፉጋ /fuga/ እየተባሉ የሚጠሩና በሸክላ ስራ የሚተዳደሩ ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡እነዚህ የማህበረሰብ አካላት በዘር ሀረግ አቆጣጠር የሀዲያ ህዝብ አካል ያልሆኑ ከመሆናቸውም በተጨማሪ አመለካከቱም የአብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አመለካከት ነጸብራቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

የሀዲያ ሴራ በመሰረቱ የሀዲያን የዘር ሀረግ የማይቆጥሩ ሰዎችን ከማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄሮች ሀዲያ /Hadiyyichcho/ አድርጐ በመቀበል የሴራ ስርአት አካል አድርጐ፣ በዘር ሀረግ ሀዲያ ከሆኑት ያለ አንዳች ልዩነት፣ ሙሉ የሴራ አባል ተደርገው የሚወሰዱበት አሰራር አለው፡፡ ይህ አሰራር በዋናነት የሚሰራው በማንኛውም ዘመን የተፈጠረውን የጋብቻ ግንኙነትን በመቁጠር የጋብቻ ግንኙነት

ውጤት የሆነውን ትውልድ በአጠቃላይ *ለንድ ኦስ* /Land ooso/ በማለት የሀዲያነትን እውቅና በመስጠትና የሀዲያን ባህላዊ ስልጣን እንኳን እኩል ተጠቃሚ በማድረግ ነው::

እላይ የተጠቀሰዉን ባህርይ የያዘው የሀዲያ ሴራ ለአጠቃላይ አሰራር እንዲያመች ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ አጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ (ምናደባ /Minaadaba/) ድረስ የተዋቀሩ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮች አሉት:: እነዚህ መዋቅሮች የየራሳቸው የስራ ድርሻ፣ መሪ፣ እንዲሁም ከሌሎች መዋቅሮች ጋር የሚኖራቸው የስራ ግንኙነት በሀዲያ ሴራ በግልጽ የተወሰነ ነው::

3.2. የሀዲያ ሴራ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት

የሀዲያ ብሄር በአምስት ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮች የተደራጀ ነው:: እነርሱም፤ *ምኔ* /Mine/፣ *ሞሎ* /Moollo/፣ *ሱሎ* /Sullo/፣ *ጊቾና* /Giichchoo/ *ጊራ* /Giira/ የተባሉ ናቸው:: ሆኖም ግን የሀዲያ ማህበረሰብ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ያለው መስተጋብር እያደገ በመምጣቱና አንዳንድ ጊዜ አንድ ተመሳሳይ የቅርብ ቅድመ አያት በሚቆጥሩ ሀዲዮች መካከል ከሌላ የሀዲያ ቤተሰብ የሚመደቡ ሰዎች አብሮ መኖር ሲጀምሩ እንደዚህ አይነት ከደም ሀረግ ጋር የማይሄድ አብሮነትን ሲያስተናግድ የሚችል ሁኔታን ለመፍጠር *ነፈራ* / Nafara/ የሚባል መዋቅር ፈጥረዋል:: በመሆኑም ከነፈራ ውጭ ከላይ የተጠቀሱት የሀዲያ ህዝብ ባህላዊ ተቋማት የደም ሀረግ ዝምድናን መሰረት በማድረግ የተዋቀሩ ናቸው::

*ምኔ፣ ሞሎ፣ ሱሎ፣ ጊቾና ጊራ* እንደቅደምተከተላቸው የሚቆጥሩት ቅድመ አያት እየራቀ፣ የሚይዙት የአባላት





ቁጥር እየጨመረ፣ የሚሳተፉበትም ሃላፊነት እየከበደ የሚሄድ ነው:: እላይ በተጠቀሰው ቅደምተከተል ውስጥ በአንዳንድ የሀዲያ አካባቢዎች "ነፈራ" በ "ምኔ"እና በ "ሞሎ"መካከል የሚገኝ መዋቅር ነው ተብሎ ሲታሰብ፤ በአንዳንዶቹ አመለካከት ከሞሎ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ስራ የሚሰራና ተመጣጣኝ ስልጣን ያለው መዋቅር ነው ተብሎ ይታሰባል:: ስለዚህ የሀዲያን ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር በቅደም ተከተል ስናስቀምጥ፤ *ምኔ፣ ነፈራ፣ ሞሎ፣ ሱሎ፣ ጊቾ፣ ጊራ* ማለት ይቻላል:: በዚህ መሰረት ለምሳሌ፣ ምኔ በጣም ጥቃቅን የማህበረሰብ ጉዳዮችን በሃላፊነት የሚከታተል ሲሆን አባላቱም አንድ አያት የሚቆጥሩ ውስን ቤተሰቦች ይሆናሉ:: "ጊራን" ብንወስድ አጠቃላይ የሀዲያን ህዝብ የሚያቅፍ በጣም ትልቁና የመጨረሻው መዋቅር ነዉ:: ከዚህ በመቀጠል በባህላዊ አስተዳደሩ ዉስጥ ያሉትን ተቋማትና ሚናቸዉን እንቃኛለን::

## 3.3. ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማትና ሚናቸው

### 3.3.1. ምኔ ወይም አበሮሳ

*ምኔ* /Mine/ ወይንም *አበሮሳ* /Abaroosa/ በጣም ትንሹ የሀዲያ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ነው:: ይህ መዋቅር አንድ አያት የሚቆጥሩ ቤተሰቦችን እንደ አባላቱ ይይዛል:: የዚህ መዋቅር መሪ ሆኖ የሚያገለግለው ታላቅ (ከቤተሰብ በእድሜ የሚበልጥ) ነው:: በተለያዩ ምክንያቶች ከቤተሰቡ በእድሜ ታላቅ የሚሆን መሪ ቤተሰቡን /ምኔን/ በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር በማይችል ሁኔታ ውስጥ ሲሆን መሪ ሲሆን የሚገባው ታላቅ ስልጣኑን በእድሜ ታናሽ ለሆኑት የቤተሰብ አባላት መርቆ ሊያስተላልፍ ይችላል::

በመሪነት ችሎታ ላይ ሳንካ ከሚፈጥሩት ሁኔታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ህመም፣ አካል ጉዳተኝነትና በጣም የበዛ እርጅና ይጠቀሳሉ፡፡ የቤተሰቡም መሪ ሆኖ የሚያገለግለው ሰው ማእረጉ ምዕን ዳና /Mi'nn Daana/ ይባለል፡፡ ምኔ በሀዲያ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ በሃላፊነት የሚወጣው ብዙም ክብደት በሌላቸውና ጥቂት የቤተሰብ አባላትን በሚያገናኙ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምኔ እንደተቋም በከባድ የማህበረሰብ ጉዳዮች በምስክርነት፣ በማጣራት፣ ወይም ከላይኞቹ መዋቅሮች የተላለፉትን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በማስፈጸም ደረጃ ይሳተፋል፡፡

ምኔ፣ ለሁለት የተለያዩ ምኔዎች አባል በሚሆኑ ግለሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ጉዳዮችን የመመልከት ኃላፊነት አሰው፡፡ ይህንን ሃላፊነት የሚወጣው የአንዱ ምኔ አባል ከሌላው ምኔ አባል ጋር ባለው ጉዳይ አንደኛው ለሌላኛው ጉዳዩ እንዲታይ ሲያመለክት ነው፡፡ ምኔ በከባድ የሀዲያ ህዝብ ጉዳዮች ከሚሳተፍባቸው አጋጣሚዎች ዋነኛው የነፍስ መጥፋትን ያስከተለ ወንጀል ተፈጽሞ ተጠርጣሪው ገዳይ ጉዳዩን ማመን ካልቻለ/ካልቻለች/ የሚከሰት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የምኔ አባላት ተጠርጣሪውን የመመርመር፣ የማጣራትና እውነቱን የማውጣጣት ኃላፊነት ሲኖርባቸው በፍጹም ወደ ማሳመን መድረስ ካልቻሉና ጥርጣሬው መሰረተ ቢስ መሆኑን ካመኑ የምኔ አባላት የተጠርጣሪውን የቅርብ ቤተሰቦች በመወከል በጉዳዩ ላይ እጃቸው እንደሌለ በመሃላ ማረጋገጥ አሰባቸው፡፡

ምኔ፣ እንደ ሀዲያ ባህላዊ አስተዳደር መዋቅር በህዝብ ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱትንና አነስተኛ ጥንካሬ ያላቸውን አለመግባባቶችንና ግጭቶችን የመፍታት ሚና በባለቤትነት ይጫወታል፡፡ በአጠቃላይ የምኔ ሃላፊነቶች ከሚባሉትና በምኔ





ደረጃ ከሚፈቱት ግጭቶች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

- በባልና በሚስት መካከል የሚከሰት ግጭት፣
- በጎረቤታሞች መካከል በጋራ ድንበር ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች፣
- በሀዲያ ሴራ ለማይገዙና ለማይታዘዙ የምኔ አባላት የምክር አገልግሎት መስጠትና የሀዲያ ሴራ ወደ ተከታዩ ትውልድ የሚተላለፍበትን መደበኛ ያልሆነና በተግባር የተደገፈ ስልጠና መስጠት፣
- በላይኞቹ የሀዲያ ሴራ መዋቅሮች የተላለፉ ውሳኔዎችን ማስፈጸም፡፡

በሀዲያ ህዝብ እምነት ማንኛውም ጉዳይ ከመሰረቱ ተጀምሮ መታየት አለበት ተብሎ ስለሚታመን ሁል ጊዜ ምኔ በማንኛውም የህዝቡ ጉዳዮች በተለይም ቀለል ባሉት ጊዜ የመጀመሪያ ደረጃ ጉዳይ የሚታይባቸው መዋቅር ሆኖ ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ምኔ፣ የሀዲያ ህዝብ እምብርት ወይም ማዕከላዊ መዋቅር ነው ማለት ይቻላል[1]፡፡

### 3.3.2. ነፈራ

የሀዲያ ሴራ ባህላዊና ማህበራዊ የአደረጃጀት መዋቅር ውስጥ ነፈራ /Nafara/ ከታች ወደ ላይ በሁለተኛ ደረጃ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ የነፈራ መዋቅር መገኛ እንደ አንዳንድ የሀዲያ ብሄር አባላት አመለካከት ከሞሎ /Moollo/ ጋር በትይዩ ሊቀመጥ እንደሚችል ይገለጻል፡፡ የነፈራ መዋቅር በአንድ መንደር የሚኖሩ ሰዎች የዝምድና ግንኙነት ታሳቢ ሳያደረግ ሁሉንም በአንድነት አባል አድርጎ የሚያቅፍ

ነው። በመሆኑም የነፈራ የአባልነት አደረጃጀት መሰረቱ በአንድ ኩታ ገጠም መልክአ ምድራዊ አካባቢ ወይም መንደር አብሮ መኖር ብቻ ነው።

ይህ ለየት ያለ የሴራ መዋቅር ሲፈጠር የቻለው የሀዲያ ህዝብ በየመንደሩ ከሌሎች በዘር ሀረግ ሀዲያ ካልሆኑት ህዝቦች ጋር ያለው መስተጋብር እየጨመረ ሲመጣና ሀዲያም ሆነው በአንድ መንደር እየኖሩና እንዳንዴ ተመሳሳይ ደጃፍ እየተጋሩ ተመሳሳይ አያትና ቅድመ አያት መቁጠር የማይችሉ ሲሆኑ የዚህ አይነት ብዙህነትን /diversity/ ለማቀፍ ነው። በመሆኑም ነፈራ የሀዲያ ህዝብ በባህላዊና ማህበራዊ የአስተዳደር ተቋሙ ብዙህነትን በመዋቅር ደረጃ አክብሮ ሌሎችን ለማቀፍና ለመሸከም ያለውን ፍላጐትና ተግባር አመልካች ነው።

የነፈራ መዋቅርና በስሩ ያሉትን የመንደሩ ተቋማት ለምሳሌ፣ እድር እና እቁብ በማንኛውም ነገር የተመሰረተ አድልዎ በነዋሪዎቹ መካከል የማያደርጉ ናቸው። በመሆኑም የነፈራ መዋቅር ለማንም አባሉ የእኩልነትን ስሜት እንዲያዳብር የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ አንድ አባል የንብረቱና የቤቱ፣የመሬቱና የሙያው ባለቤት ስለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ ነው። በአባላት ተሳትፎ ደረጃም ሲለካ በማንኛውም የውሳኔ አሰጣጥ አባላቱ በንቃት የሚሳተፉበት ሲሆን፣ አባላቱ የነፈራን ጥቅሞች ለምሳሌ የግጦሽ መሬት፣ ውሃ፣ የገበያ ስፍራና ሌሎችንም እኩል ሲጋሩ በነፈራ ስም በሚቋቋሙት ተቋማት /ለምሳሌ፣ እድርና እቁብ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ ይሆናሉ። ከዚህ በተጨማሪ የአንድ ነፈራ አባላት በአጠቃላይ የአካባቢውን ችግር በጋራ የመወጣትም ሀላፊነት አለባቸው።





ነፈራ እንደ ሀዲያ ህዝብ ባህላዊና ማህበራዊ የአስተዳደር ተቋምነቱ ዝቅተኛ መጠን ያላቸውንና በአባላቱ መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን የመፍታት ሃላፊነት አለበት። ይህንን በማድረግም በአባላቱ መካከል ሰላምንና ተጣጥሞ መኖርን ያበረታታል። በዚህ የነፈራ ተቋም አማካኝነት ለምሳሌ፣ በአባላቱ መካከል የሚከሰቱ የድንበር ግጭቶች፣ በግጦሽ መሬት ሰበብ የሚከሰቱ አለመግባባቶችና በእድርና በእቁብ ምክንያት የሚከሰቱ ልዩነቶችና ግጭቶች እንዲሁም የተበደሩትን ገንዘብ ወይም የተዋሱትን እቃ ወይም ንብረት በአግባቡ ከአለመክፈል ወይም ከአለመመለስ ጋር የተያያዙ ግጭቶችና አለመግባባቶች ይታያሉ፤ መፍትሄ ይሰጥባቸዋል።

እላይ ከተጠቀሱት ሀላፊነቶች በተጨማሪ ነፈራ ከሌሎች የላይኛው መዋቅሮች የተላለፉ ውሳኔዎችን እንዲያስፈጽም ሲጠየቅ ይተገብራል። በአጠቃላይ የነፈራ መዋቅር መሰረታዊ ሀላፊነት በአባላቱ መካከል ማህበራዊ መረዳዳትንና መግባባትን ማበረታታትና መከታተል ይሆናል።

የነፈራ መሪ ማዕረግ ነፈዕል ዳና /Nafa'l Daana/ በመባል ይጠራል። ነፈዕል ዳና በነፈራው ወንድ ጐልማሳ አባላት ጉባኤ ይመረጣል። አንድን ግለሰብ ነፈዕል ዳና አድርጐ ለመምረጥ ታሳቢ ከሚደርጉት መስፈርቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤ የግለሰቡ የብስለትና የእውቀት ደረጃ እና የአካባቢውን ማህበረሰብ የመምራትና የማስተባበር ብቃት ናቸው። በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት መሠረታዊ መስፈርቶች ልቆ የተገኘ ማንኛውም የነፈራ አባል ነፈዕል ዳና መሆን የሚችል ሲሆን ማዕረጉና ስልጣኑ ከደም ሀረግና ከእድሜ ጋር ያልተያያዙ ናቸው። እንዲያውም አንድ ነፈዕል ዳና ተደርጐ የተሾመ ግለሰብ አባላቱ ተገቢ ነው ብለው

በሚያምኑበት በማንኛውም ምክንያት ሀላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ካቃተው የአባላቱ ጉባኤ ግለሰቡን ከስልጣኑ ያነሳዋል፡፡ ስለዚህ የነፊዕል ዳና ስልጣን የሚቆየው አባላቱ በመሪው ላይ እምነት እስካላቸው ጊዜ ድረስ ብቻ ነው፡፡

ነፊራ በአባላቱ የሰርግ ስነ- ስርአት፣ በለቅሶና በሀዘን ወቅት ከፍተኛ ተሳትፎ ያለው ሆኖ ማንኛውንም አስተዋጽኦ በማበርከት ከባለጉዳዩ አባል ጉን መሆኑን ያስመሰክራል፡፡ በሰርግ ስነ- ስርአት ለምሳሌ፣ ከእንጨት ፈለጣ ጀምሮ እስከ ማስተናገድ ድረስ ያለውን የጉልበት ስራ የነፊራ አባላት ይሰራሉ፡፡ በለቅሶም ወቅት ማንኛውንም የጉልበት ስራ ከመስራት በተጨማሪ በእድር አማካይነት ሰሰቅሰው አስፈላጊ የሆኑ የመገልገያ እቃዎችን ያቀርባሉ፤ የማጽናናት ሃላፊነትንም ይወጣሉ፡፡

### 3.3.3. ሞሎ

ሞሎ /Moollo/፣ በሀዲያ ባህላዊና ማህበራዊ የአስተዳደር መዋቅር መሰረት ከአንድ በላይ ምኔዎች /Minneewwa/ የሚመሰርቱት ተቋም ነው፡፡ የተለያዩ ምኔዎች ተመሳሳይ ቅድመ-አያት የሚቆጥሩ ሲሆን አንድ ላይ በመሰባሰብ አንድ ሞሎን /Moollo/ ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም የአንድ ሞሎ መሠረታዊ አባላት ተብለው የሚታሰቡት ሞሎን የመሰረቱት እና ከአንድ በላይ የሆኑ ምኔዎች ይሆናሉ፡፡

በሀዲያ ማህበረሰብ ውስጥ በጣም እንደተለመደው እጅግ አብዛኛው የአንድ ሞሎ አባልነትን የሚጋሩ ግለሰቦች በአንድ ኩታ ገጠም በሆነ መልክአ ምድራዊ አካባቢ ሰፍረው ይኖራሉ፡፡ ሞሎ በሀዲያ ባህል መሰረት በምልዳና





/Mooll Daana/ የሚመራ ተቋም ሲሆን በምንም ምክንያት ይህ ስልጣን የሞሎ አባል ላልሆነ ግለሰብ አይሰጥም፡፡ አንድን ግለሰብ ሞልዳና አድርጐ ለመምረጥ መሰረታዊ መስፈርት ተደርጐ የሚወሰደው የግለሰቡ የመምረት ብቃትና ችሎታው ነው፡፡ ይህንን የመምረጥ ብቃትና ችሎታን አመልካች ናቸው ተብለው ከሚታሰቡት ዝርዝር መስኪያዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ግለሰቡ የማህበረሰቡን የተለያዩ ጉዳዮች ከተለያዩ ጐኖችና አቅጣጫዎች የመረዳት ብቃትና የተረዳውን ነገር በተገቢው መንገድ የመግለጽና የማስረዳት ችሎታ፣
- በአንድ ሞሎ አባላት መካከልና ራሱ አጠቃላይ ሞሎ ከሌሎች የሀዲያና የአካባቢው ህዝቦች ጋር ያለውን የደም ዝምድናና የጋብቻ ትስስር ጠንቅቆ የማወቅ ብቃት፣
- በሀዲያ ሴራ እና በአፈጻጸሙ ላይ ያለው ጠንካራ እውቀት፤ ለምሳሌ፣ በሀዲያ ሴራ ውስጥ ተዋቂ ከሆኑ የአፈጻጸም ጉዳዮች ውስጥ አንጐኦ /Ango'o/፣ ዊሪቾ /Wiriichcho/፣ ጐራ /Goora/ እና በመሳሰሉት ላይ ያለውን እውቀት ይመለከታል፡፡
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ችሎታ፣

የሞሎ ትልቁ ተግባር ተደርጐ የሚወሰደው በምኔ እና በነፊራ ደረጃ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው በውሳኔው ቅሬታ ያለው ወገን የሚያቀርበውን የይግባኝ ጉዳዮች መመልከትና በታችኞቹ እርከኖች (Mine እና Nafara) መፍትሄ ማግኘት ያልቻሉ ጉዳዮችን መዳኘት ነው፡፡

ሞሎ በራሱ ውስጥ ባሉት በሁለት ምኔዎች መካከል የሚከሰቱ ማንኛውንም ጉዳዮች በቀጥታ የመመልከት ስልጣን አለው፡፡ ምንም እንኳን ሞሎ በርካታ የግጭት አይነቶችን መዳኘት ቢችልም ሞትን ያስከተለ ግጭት ከሆነ ግን የመጨረሻ ውሳኔ አይሰጥም፡፡ የሞትን ጉዳይ ውሳኔ ከመስጠት ውጭ የመዳኘት ስልጣኑን ጨምሮ ሞሎ የሚከተሉት ስልጣኖች አሉት፡፡

- የቤት ቃጠሎን ያስከተለ ግጭትን መፍታት
- ለእንያዳንዱ ምኔ የሞት ካሳ ቅጣትን ለመክፈል የሚደርሰውን ድርሻ /Ango'o/ ማከፋፈል
- ለእንዳንዱ ምኔ የሹመት ስነ-ስርዓትን /Mahallano/ ለማክበር የሚያስፈልገውን ወጪ /Wiriichcho/ ማከፋፈልና የመሳሰሉ ከባድ ሀላፊነቶችን መወጣት፡፡

ሞሎ አባላቱ በሆኑ ምኔዎች መካከል የሚታየውን ፉክክርና ጠንካራ ምኔ በደካማው ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ ይከላከላል፡፡ በዚህም ተግባሩ ሞሎ በሁሉም ምኔዎች መካከል የእኩልነትንና የመከባበር ስሜት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

### 3.3.4. ሱሎ

*ሱሎ* (Sullo) በሀዲያ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ከሞሎ ቀጥሎ የሚገኝ ሲሆን አንድ ሩቅ ቅድመ አያትን በጋራ የሚቆጥሩ በርካታ *ሞሉዎችን* (Moolluwwa) በአንድ ላይ አቅፎ የሚይዝ መዋቅር ነው፡፡ በመሆኑ ዋነኞቹ የሱሎ አባላት ተብለው የሚወሰዱት *ሞሉዎች* ናቸው፡፡





የሱሎ መሪ ልክ እንደ ሞሉ የራሱ አባል ከሆኑ ሱሎዎች መካከል የሚመረጥ ሲሆን የመሪውም ማዕረግ *ዳና* (Daanna)፣ *ወሻባ* (Woshaaba)፣ *ዳድቾ* (Daadichoo)፣ *ሀሰልቾ* (Hasallichcho) ወይም *መጋባ* (Magaaba) ሊሆን ይችላል፡፡ አንድን ግለሰብ የሱሎ መሪ አድርጐ ለመምረጥ የሚታዩ መስኪያዎች ከሞሎ መሪ ከሚጠበቁት ጋር ተመሣሣይነት አላቸው፡፡ የሴራ እውቀት እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ችሎታ በዋናነት ከሱሎ መሪ *(ሱል ዳና* /Sull-daanna/) የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው፡፡

ሱሎ አባላቱ በሆኑ ሞሉዎች መካከል የሚከሰቱትን ግጭቶችንና አለመግባባቶችን የመፍታት ሥልጣን አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሞሎ መዋቅር አልፈው የሚመጡ ማንኛውንም የይግባኝ ጉዳዮችን የማየትና ውሳኔ የመሥጠት ሥልጣን አለው፡፡ የሱሎ መዋቅር የነፍስ መጥፋት ወንጀልን ወይም የነፍስ ማጥፋትን ያስከተለ ግጭት የማየት፣ የመመርመርና፣ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያለው መዋቅር ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ሥልጣን መጠቀም የሚችለው ጉዳዩ የተፈጸመው የራሱ አባላት በሆኑ ሞሉዎች መካከል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ሱሎ እንደ አንድ የሀዲያ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር ተቋም በሀዲያ ውስጥ የዝምድና ጋብቻን የመከላከል ኃላፊነት አለበት፡፡ በሀዲያ ባህል መሠረት በሱሎ አባላት መካከል ጋብቻ መፈጸም ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በአባትም ሆነ በእናት ወገን እስከ ሰባት አባት በሚጋሩ ግለሰቦችና ጋብቻ የሚከለከል መሃላ (*ሀድሮ* / Hidiro/) በፈጸሙ ቤተሰቦች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጸም ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር በማድረግ ይከለክላል፡፡

### 3.3.5. ጊቾ

*ጊቾ* (Giichcho) በሀዲያ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ተመሳሳይ የሩቅ ቅድመ አያትን በጋራ የሚቆጥሩና ከአንድ በላይ የሆኑ *ሱሎዎች* (Sullewwa) የሚመሰርቱት ተቋም ነው፡፡ በመሆኑም ጊቾ አባላቱ አድርጐ የሚያቅፋቸው የተለያዩ *ሱሎዎችን* ነው፡፡

በሀዲያ ባህል መሠረት የጊቾ መሪ በተለያዩ የሀዲያ አካባቢዎች የተለያዩ ማዕረጐችን ይይዛል፡፡ ከነዚህም ማዕረጐች ውስጥ *አንጃንቾ* (Anjaancho)፣ *አባገዳ* (Abaagada)፣ *ዳና* (Daana)፣ *ገራዳ* (Garaada) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በአፈ ታሪክ አዋቂ የሀዲያ አዛዉንት እምነት *ገራዳ* (Garaada) የሚለው ማዕረግ ለመሪ የሚሰጠዉ ከጊቾ መዋቅር ጀምሮ ነው፡፡ አንድ ግለሰብ የጊቾ መሪ ሆኖ ከላይ ከተጠቀሱት ማዕረጐች አንዱን ለመያዝ የሀዲያ ባህል ካስቀመጣቸው መሠረታዊ መሥፈርቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ[49] የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን የተለያዩ ጉዳዮች በጥንቃቄ የመመርመር፣ የመተንተንና የመረዳት ጥበብ ያለው፡፡
- ከምርመራው ትንተናና የመረዳት ጥበብ በመነሳት ወደፊት የሚከሰተውን ሁኔታ የመተንበይ ወይም የማላየት ችሎታ ያለው፡፡
- በቂ ሀብትና ንብረት፣ ሰፊ ደጃፍና ቆንጆ ቤቶች ያሉት ሆኖ ብዙ እንግዳና ባለጉዳይ የማስተናገድ አቅም ያለው፡፡
- ትንቢትን /Hiraaga/ የመረዳትና የመፍታት ብቃት ያለው፡፡

[49] በሀዲያ የገራዳነት መእረግ ሲሰጥ ሀራጋ /Hiraaga/ መቻል መሰረታዊ መስፈርት ሆኖ ያገለግል እንደነበረ ከዝርዝሩ መረዳት ይቻላል፡፡





ጊቾ እንደ ሀዲያ ህዝብ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር አንድ በግለሰብ አማካይነት በቀጥታ የሚቀርብለት ማንኛውንም ጉዳይ ተቀብሎ ለማስተናገድ ይቸገራል፡፡ ለዚህ ሁኔታ መሠረታዊ ምክንያት ተደርጐ የሚወሰደው የጊቾ ግለሰብ አባላት እጅግ ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ዕድሉ ቢሰጥ የሚቀርብለት ጉዳይ ብዛት መዋቅሩን የማያሰራ ሊሆን ስለሚችል ነዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ከጊቾ በታች ያሉት መዋቅሮች ዕለት ዕለት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን የተለያዩ ጉዳዮች እንዲያዩና በተቻለም መጠን እንዲፈቱ ምቹ ሆኔታን በመፍጠር ታችኞቹን መዋቅሮች ለማጠናከርና የስልጣን ክፍፍሉን እስከ እያንዳንዱ መንደር ድረስ በፍተሃዊነት ለመከፋፈልም ተብሎ ነው፡፡በመሆኑም የግለሰብ ጉዳዮች በጊቾ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ሊታይና ሊፈታ የሚችለው ጉዳይ ከሱሎ በይግባኝ (ህጎኦ /Higo'o/) ፈቃድ የመጣ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

የጊቾ መሠረታዊ ሃላፊነት ተብሎ የሚወሰደው በሁለት ሱሎዎች መካከል የሚከሰቱ ጉዳዮችንና ግጭቶችን መመርመርና መፍታት ነው፡፡ ከዚም በተጨማሪ ጊቾ የነፍስ መጥፋትን ያስከተለ የወንጀል ጉዳይን የመመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት አለበት፡፡ የነፍስ መጥፋትን ያስከተለ ወንጀል ጊቾ ተቀብሎ የሚመረምርበት ምክንያት ምንም እንኳን ወንጀል ፈጻሚው አንድ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ቢሆኑም እንደነፍስ ማጥፋት ያሉ የወንጀል ጉዳዮች የአጠቃላይ ህዝብ ሃላፊነቶች ተደርገው ስለሚታሰቡ ነው፡፡

በሀዲያ ሴራ አንድ ግለሰብ የፈጸመው ጉዳይ ተጣርቶ ቅጣት ሲወሰንበት ቅጣቱን ተቀብሎ የማይፈጽምና ከስህተቱ

የማይስተካከል ሲሆን ግለሰቡ ከማንኛውም ማህበራዊና ባህላዊ ተሣትፎዎች እንዲገለልና ማህበራዊና ባህላዊ ተቋማትን እንዳይገለገል ገደብ ሊጣልበት ይችላል። ይህም ገደብ ያይማ /Yaayyimma/ በመባል ይታወቃል። ይህ ዓይነት ግለሰብ በጊዜ ሂደት ስህተቱን አምኖ ይቅርታ ሲጠይቅና ቅጣቱን ሲፈጽም ለግለሰቡ ይቅርታ በመስጠት ከማህበረሰቡ እንዲቀላቀል ፈቃድ የሚሰጠው ጊቾ[50] ነው።

ጊቾ ከላይ ከተጠቀሱት ሃላፊነቶች በተጨማሪ ለራሱ አባላት የሚያገለግሉ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና፣ ፖለቲካዊ ፖሊሲዎችንና አቅጣጫዎች ማስተዋወቅ፣ በአባላቱ ላይ በማንኛዉም የውጭ ሃይሎች የሚደርሰውን ተፅዕኖ የመከላከልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥት ጋር አብሮ በመሥራት ችግሮችን የመፍታት፣ የአንድ ጊቾ አባል የሆኑና በተለያዩ አካባቢዎች ተበታትነው የሚኖሩት ግለሰቦችንና ቡድኖች ማፈላለግና ማስተዋወቅ በዋናነት ይጠቀሳሉ። በአጠቃላይ ጊቾ በጣም ከባድ በሆኑ የህዝቡ ጉዳዮች የሚሳተፍና ውሳኔ የሚያስተሳልፍ መዋቅር ነው።

### 3.3.6. ጊራ


ጊራ /Giira/ የሀዲያ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር አጠቃላይ የሀዲያን ህዝብ (ምናደባ /Minaadaba/) የሚያቅፍና የመጨረሻዉ ቅልቁ መዋቅር ነዉ። ምንም እንኳን እንደ አብዛኞቹ የሀዲያ አዛውንት ይህ መዋቅር በየዕለቱ የሚሰራና የራሱ የሆነ ቋሚ መሪ ያለው ባይሆንም የአጠቃላይ የሀዲያን ህዝብ በሚመለከቱ ጉዳዮች ለምሳሌ ጦርነት፣ የግብር

50 ያይማ በጊቾ ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የአባላቱ ብዛት በተገለለዉ ግለሰብ የሚያስከትለዉ የስነ-ልቦናና ማህበራዊ ጫና ታሳቢ ተደርጎ ሊሆን ይችላል።





መብዛት፣ ድርቅና ረሃብ በአንድነት ህዝቡን የሚመሩ ግለሰቦች የተለያዩ ማዕረጎች ይይዛሉ። እነዚህ የጊራ /Giira/ መሪዎች ከሚይዟቸው ማዕረጎች ማካከል እማማ /Imaarna/፣ አድላ /Adila/ እና ገራዳ /Garaada/ በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። ስጊራ መዋቅር ከላይ የተጠቀሱትን ማዕረጎች የሚይዝ አዲስ መሪ የሚመረጥ ሳይሆን ከጊቾ መሪዎች መካከልና ድሮም ከማዕረጎቹ አንዱ ከተሰጣቸው ግለሰቦች እንደወቅቱ ሁኔታ የጊራንም መሪነት እንዲይዝ የሚደረግ ይመስላል።በአጠቃላይ የሴራ መዋቅር[51] ከላይ ወደታች እንደሚከተሰው በቻርት[52] መልክ ማስቀመጥ ይቻላል።




51 ክላይ የተመለከተዉን መዋቅር የነደፉት አቶ አሰፋ ቡንጤ እና አቶ ታገለ ኤረንጎ ናቸዉ።

52 የቻርቱ ቀስት የሚያመለክተዉ የተጠያቅነት አቅጣጫን ነዉ።

## 3.4. ግጭትና የግጭት አፈታት በሀዲያ ሴራ

### 3.4.1. የግጭት ምንነት፣ ዓይነቶችና ደረጃዎች

በሀዲያ ሴራ ግጭት፣ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች መካከል ለምሳሌ፤ በቤተሰብ አባላት፣ በባልና በሚስት፣ በጐረቤታሞች፣ ሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ምኔዎች /Minnewwa/፣ በሞሎዎች /Mollowwa/ ወዘተ. መካከል የሚከሰት አለመግባባት ነው፡፡ የአለመግባባቱ መሰረታዊ መነሻ የሚሆኑ የፍላጐት፣ የአመለካከትና የምርጫ ልዩነቶች ሲሆኑ ይችላሉ፡፡ የግጭት ዓይነቶችና ደረጃዎች በተሳታፊ አባላት መጠንና ዓይነት፣ በግጭቱ ወቅት ጥቅም ላይ በዋሉት መሳሪያዎች ዓይነትና ብዛት እና ግጭቱ ባስከተለው ጉዳትና ጥፋት ዓይነትና መጠን ይከፋፈላል፡፡

በሀዲያ ሴራ ግጭቶች በአምስት ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፋፈላሉ፡፡ የመጀመሪያው ትንሹ የግጭት ዓይነት *ቱኩሮኦ* /Tukuro'o/ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ የግጭት ደረጃ በጣም ቀዝቃዛ የሆነና ስርኣት ባለው ሁኔታ ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች አለመግባባታቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በዚህ የግጭት ደረጃ የተጋጮቹ የስሜታዊነት ደረጃ ዝቅተኛ ነው፡፡ በግጭቱ መሰዳደብና እና መናቆር *(ዱእመንቻ ወይንም ገሜእለንቻ /* Du'mmanchcha te'm gamellancha/) በዋነኛነት እንደ መሳሪያ ያገለግላሉ፡፡

*ፋጮኦ* /Facco'o/ ሁለተኛ ደረጃ ግጭት ሲሆን በዚህ ደረጃ ተጋጭ ቡድኖች ስሜታዊነት በተሞላበትና ስርኣት በሌላው ሁኔታ የቃላት ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ምንም እንኳን የአካል ግጭትን ባያስከትልም ጥንቃቄና የቅርብ ክትትል ካልታከለበት





ወደ ከፍተኛ ደረጃ የአካል ግጭት ሊያመራ የሚችል የግጭት ደረጃ ነው፡፡ *በፊጮኦ* ዋነኛ የግጭቱ መሳሪያ ስድብና ዘለፋ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተገለጹት ሁለቱ ደረጃዎች በግጭት ወቅት ስራ ላይ የሚውለውን መሰረታዊ መሳሪያ ማለትም መሰዳደብና መዘላለፍን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሀዲያ ሴራ የቃላት ግጭት (*ሱእም ጀናንቻ* /Suu'm Jannancha/) ወይም (አፍ ጠለፋ /Afi xalafa/) ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

በሀዲያ ሴራ መሰረት ሶስተኛ ደረጃ የሚይዘው ግጭት *ጉርጉያቶ* /Gurguyyaatto/ ተብሎ ይጠራል፡፡ *የጉርጉያቶ* ደረጃ ያለው ግጭት በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች መካከል ሲከሰት ከቃላት ግጭት አልፎ መጠነኛ ጉዳት የሚያስከትልና አነስተኛ ውጤት የሚያመጡ መሳሪያዎችን ያካተተ አካላዊ ግጭትን ያቀፈ ነው፡፡ ጉርጉያቶ በተለይም በትልልቅ ቡድኖች መካከል በምከሰትበት ጊዜ አካላዊ ግጭቱ ረጅም ስአት ሳይቆይና ብዙ የንብረትና የአካል ጉዳት ሳያስከትል በፊት በቁጥጥር ስር ይውላል፡፡

*ታምበከሳ* /Tambakasa/ ወይም *ደምበቃ* /Dembaqa/ አራተኛው ከፍተኛው የግጭት ደረጃ ነው፡፡ ይህንን ደረጃ የደረሰ ግጭት ሁል ጊዜ ሊከሰት የሚችለው በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ትልልቅ ቡድኖች መካከል ሲሆን ማንኛውም የተጋጭ ቡድኖች አባል የሆነ ግለሰብ የቡድኑን ጥቅምና ፍላጐት ለማስከበር በግጭቱ ይሳተፋል፡፡ በመሆኑ የግጭቱ ተሳታፊ ለመሆን የቡድኑ ለምሳሌ፣ የሱሉ ወይም ሞሎ አባልነት ብቻውን እንደ መስፈርት ሊያገለግል ይችላል፡፡ *ታምበከሳ* ወይም *ደምበቃ* ሲከሰት በግጭት ውስጥ ያሉ ቡድኖች

ተቃራኒያቸውን ለማጥቃት ያላቸውን ማንኛውንም ከፍተኛ አቅምና መሳሪያ ይጠቀማሉ። በመሆኑ ይህን ደረጃ የደረሰ ግጭት የሚያስከትለው የንብረት ውድመትና የህይወት መጥፋት ከፍተኛ ሆኖ የተሳታፊዎችም ቁጥር በጣም ብዙ ይሆናል።

የመጨረሻውና እጅግ ከፍተኛው የግጭት ደረጃ *ኦራ* /Ora/ ይባላል። በሀዲያ ሴራ *ኦራ* /Ora/ አጠቃላይ ጦርነት ማለት ነው። ይህ ግጭት በዋናነት የሀዲያ ብሄር ከሌሎች ህዝቦችና ሀይሎች ጋር ግጭት ውስጥ ሲገባ የሚከሰት ነው። እንደ ማንኛውም ጦርነት ዝግጅት፣ ድርጅት፣ አመራርና ታክቲክ የታከለበት ግጭት ሆኖ ጉዳቱና የተሳታፊዎች ብዛት ከፍተኛ ነው።

በሀዲያ ሴራ መሰረት *ጉርጉያቶ* ፣ *ተምበከሳ* ፣ *ደምበቃ* እና *ኦራ* በአንድ ላይ አካላዊ የግጭት ደረጃዎች (*አንግ ሀጎዕ ጀናንቻ* /Angi higo'o janancha/) ተብለው ይጠራሉ።

የሀዲያ ሴራ ግጭቶችን በሁለት የተለያዩ ዓይነቶች ይመድባቸዋል። እነርሱም ሀዲያ እርስ በርስ የሚያደርጋቸዉ /Intra-ethnic/ ግጭቶች እና የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች ሀዲያ ካልሆኑት ህዝቦችና ሀይሎች /Inter-ethnic/ የሚያደርጋቸዉ ግጭቶች ናቸው።

በዘመናዊው ዘመን (modern era) እንኳን የሀዲያ ብሄር በተለያዩ ምክንያቶች የተለያየ መጠን ያላቸውን ግጭቶች ሀዲያ ካልሆኑ አጎራባች ህዝቦችና ሀይሎች ጋር አድርጓል። ከእነዚህም ውስጥ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ግጭቶችን ከወላይታ፣ ከከምባታ፣ ከስልጤ ከጉራጌ እና ከአማራ ነፍጠኛ ሰፋሪዎች ጋር አድርጓል።





እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱም የግጭት ዓይነቶች የየራሳቸው መለያ ባህርይ አላቸው። ከእነዚህ መለያ ባህርዮች ዋነኛ ተብሎ የሚጠቀሰው ግጭቶቹ የሚያስከትሉት የጉዳት መጠን፣ በግጭት ወቅት ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚችሉ መሣሪያዎቹ፣ የግጭቱ አፈታት ሁኔታና ግጭቱን የሚፈቱ አካላት ናቸው።

በአብዛኛው ሀዲያ ውስጥ የሚደረጉት የእርስ በርስ ግጭቶች የሚያስከትሉት የጉዳት መጠን አነስተኛ ሲሆን በግጭት ወቅትም ጥቅም ለይ የሚውሉት መሳሪያዎች ቀላልና የሰውነት አካልን ወግተው የማይገቡ ይሆናሉ። የዚህ አይነቱ ግጭት በቀላሉ መፍታት የሚቻል ሲሆን በግጭቱ አፈታትም በየደረጃው ያሉ የሀዲያ ሴራ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት ያለ ሶስተኛ ወገን ጠልቃ ገብነት ይሳተፋሉ።

የሀዲያ ብሄር ከሌሎች አጎራባች ህዝቦችና ሀይሎች ጋር ግጭት ውስጥ በሚገባበት ወቅት የግጭቱ ደረጃም ወደ ኦራ ስለሚያድግ በግጭት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ መሳሪያዎች እጅግ አደገኛ ስለሚሆኑ ግጭቱ የሚያስከትለው ጉዳትም በጣም ከባድና አደገኛ ይሆናል። እንደነዚህ ዓይነት ግጭቶች ሁልጊዜ የሶስተኛ ወገንን ጣልቃ ገብነት ስለሚጋብዙ የአፈታቱ ሁኔታ በጣም ውስብስብና ጊዜ የሚፈጅ ይሆናል። በእነዚህ ግጭቶች ወቅት በሶስተኛ ወገንነት ከሚሳተፉ አካላት መካከል መንግስትና በግጭት ወቅት የገለልተኝነት ሚና የተጫወተ ማንኛውም የአካባቢ ብሄር ይገኙበታል።